# የትግራይ ጥንታዊ ግዛቶች ከታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ እና ነባራዊ ሁኔታ፣

## Tigray territory from history, politics, and logical perspective

ከ

አሰፋ ስዩም (Assefa Seyoum) እና ሙሉ ሸዊት (Mulu Shewit)

ይህን ፅሁፍ የትግራይ ህዝብ ታሪክ: ጥንታዊ ግዛቶች እና መጭው እጣ ፈንታ በሚል እየተዘጋጀ ካለው መፅሃፍ ኩፋለ መፅሃፍ (Chapter book) የተወሰደ ነው:: ስለዚህ ለማንኛውም ሰው ወይም አንባቢ ሂስ ክፍት ነው:: ለማንኛውም ጥያቄ እና ሂስ ደግሞ በነዚህ አደራሻዎች ማቅረብ ይቻላል::

assefaherm@yahoo.com and mulugeta.bihon@yahoo.com

ማውጫ


1. ጥንታዊ የትግራይ /የአብሲንያ/ ግዛቶች ከ15ኛው ክፍለዘመን በፊት፣
2. ጥንታዊ የትግራይ ግዛቶች በ16 ኛው ክፍለ ዘመን፣
3. ከአፄ ምኒልክ በፊት የትግራይ ጥንታዊ ግዛቶች እና ወሰን በውጭ ጸሐፊዎች ዕይታ፣
4. ከአፄ ምኒልክ በፊት የትግራይ የግዛት ወሰን፣
5. *በአፄ ሚኒሊክ ተቆርሶ ወደ ጎንደር የተካለለው የትግራይ የግዛት ወሰን*
6. በአፄ ኃይለስላሴ የተወሰዱ የትግራይ ግዛቶች፣
7. ወደ ወሎ የተጠቃለሉትን የአካቢው ህዝብ (ተጋሩ) ተቃውሞና የፅሁፍ ማስረጃዎች
8. በዘመነ ደርግ የትግርኛ ተናጋሪ ህዝብ አሰፋፈር፣
9. የኢትዮጵያ ግዛት አከላለል በተለያዩ መንግስታት እስከ ኢህአዴግ እውነታዎችና ስህተቶች፣
10. የትግራይ ግዛት አከላለልና በዘመነ ኢህአዴግ የተፈፀሙ ስህተቶች፣
11. የአማራና ትግራይ ድንበር የሆነው የግጨው ጥያቄ እንዴት ተነሳና ተፈታ፣

# ምዕራፍ አራት

## የትግራይ ጥንታዊ ግዛቶች ከታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ እና ነባራዊ ሁኔታ፣

የትግራይ እና የአብሲንያን ግዛቶች ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁኗ ዘመናዊት ኢትዮጵያ ያለውን ለማስቀመጥና ለመዘርዘር የተለያዩ ሰነዶች፣ ማስረጃዎች እና ካርታዎች ከተለያዩ ምንጮች በተለይም ደግሞ የፕሮፌሰር ገላውዴዎስ አርኣያ፣ አቶ ሓዱሽ ረዳ፣ ፕሮፌሰር ያን ኒሰን ወዘተ... መጽሐፍትና ያልታተሙ ጽሑፎችን የተጠቀምን ሲሆን፣ በድህረ-ገፅ (web-site) ከወጡት እና ጠቃሚ ሆነው የተገኙትን ማስረጃዎች ደግሞ በአይጋ ፎረም (aiga forum) የህዳሴ ኢትዮጵያ እና ሆርን አፌርስ (horn affairs) ደግሞ የአቶ ዳንኤል ብርሃነ እና የሌሎችንም ተጠቃሚ ማስረጃዎች ተጠቅመናል፡፡

### 4.1. ጥንታዊ የትግራይ /የአብሲንያ/ ግዛቶች ከ15ኛው ክፍለዘመን በፊት፣

ትግራይ ወይም አብሲንያ ከሶስት ሺ ዓመታት በላይ የዘለቀ ዕድሜ ጠገብ የመንግስትነት ታሪክ ያላት ቢሆንም የአሁኗ ኢትዮጵያ ያላት ቅርፅ የያዘችው ግን በዘመነ አፄ ምኒልክ ከ120 ዓመታት በፊት ጀምሮ እንደሆነ የታሪክ መዛግብት ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ የጥንት የትግራይ ወይም አብሲንያ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን በፊት የነበሩት ካርታዎች በአብነት እንመልከት፡-




*ካርታ 1. ጥንታዊ የትግራይ/አብሲንያ ግዛት: This map, dating from the 1570s, still takes Europe's devout wishes for geopolitical truth. It was produced in Antwerp by Ortelius, entitled A Description of The Empire of Prester John, Also Known as the Abyssinian Empire*

ከዚያ በፊት የነበረውን የግዛት ወሰን ሲታይ አንዴ የሚሰፋ ሌላ ጊዜ የሚጠብ የነበረ እንደሆነ ጥንት የትግራይ/ የአቢሲኒያ ካርታዎች ያሳያሉ፡፡ አንድ ወቅት እስከ

መካከለኛው አፍሪካ የሚለጠጥ የነበረ ሲሆን በሌላ ጊዜ ደግሞ እስከ ባህር ማዶ የመን ድረስ በመዝለቅ ግብር ይሰበሰብ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡




*ካርታ 2. ጥንታዊ ለትግራይ/ለአብሲንያ ግብር የሚገብሩ ቀይ ባህር ማዶ (የመን) ቦታዎች*


በቅርቡም የበልጄም ተወላጅና ተመራመራ የሆኑት ፕሮፌሰር ያን ኒሰን (Jan Nyssen) ጥንታዊ የትግራይ /አብሲንያ/ ካርታ ከተቀበረበት በማውጣት የትግራይ ጥንታዊ ግዛቶች በዝርዝር አመላክተዋል፡፡ ፕሮፌሰር ያን ኒሰን (Jan Nyssen) በቅርቡ ያሳተሙትን የምዕራብ ትግራይ ግዛቶች ከጥንትም ጀምሮ በትግራይ ግዛት ስር እንደበሩ መረጃ አስደግፈው አቅርበዋል፡፡ ይህንን ካርታ ጥንት የትግራይ ግዛት ከቀይ ባህር ጀምሮ እስከ መተማ አካባቢ እንደነበር ያሳያል፡፡ Belgian political Geography scholar offers compelling analysis why Amhara state claims over western Tigray are “spurious” unsupported by colonial cartography and ethno-linguistic settlement patterns. Unearthed evidence maps out Western Tigray Dispute, 13 May 2020 by Jan Nyssen.




*ካርታ 3. Unearthed evidence maps out Western Tigray Dispute, Ethiopian insight (ethiopia-insight.com)*

## 4.2. ጥንታዊ የትግራይ ግዛቶች በ16 ኛው ክፍለ ዘመን፣

ኢትዮጵያ የምትባል አገር በዓለም ካርታ ወይም በዓለም መዝገብ የሰፈረችው በትግራይ (በአክሱም) ታሪክ መሆኑን የማይታበል ሀቅና ሀቅ ነው፡፡ ከአክሱም ዘመነ መንግስት በፊትም አልፎ አልፎ በታሪክ መዛግብት ቢገኝም በዋነኝነት ጎልቶ የወጣው ግን በአክሱም ዘመነ መንግስትና ነገስታቱ በሚያደረጉት የንግድ ወይም የጦርነት ልውውጥ ነው፡፡ የአክሱም ዘመነ መንግስት ጠንከራ መንግስት ስለነበር የግዛት ማስፋፋት በተለያየ አቅጣጫ እየጨመረ ብዙ ቦታዎችን ያካትት ነበር፡፡ ትግራይ እየተባለ የሚጠራው ደግሞ የአክስማውያን ግዛት እንዱ ሆኖ ብዙ አካባቢዎች የአሁኑ ጎንደር፣ ዓፋር፣ ኤርትራን ቀይ ባሕርን ያጠቃልል እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ ለምሳሌ Manoel Barradas የተባለ የታርክ ጸሐፊ በ 1624 ዓ.ም ትግራይ ውስጥ ይኖር የነበረ የፖርቱጋል ልኡካን መሪ በ Tractatus Tres Historico-Geographici (1634) በሚል መጽሐፉ የትግራይ ካርታ በአክሱም ዘመነ መንግስት እንደዚህ አስቀምጦት ነበር፡፡ የዚያን ግዜ የትግራይ ካርታ የሚያጠቃልለው፣ በሰሜን ኤርትራ እስከ ቀይ ባህር፣ በምስራቅ አፋር ደናኬል ሸለቆ (Danacale depression)፣ በምዕራብ ወልቃይትና ሰሜን ተራሮች፣ በደቡብ የአለውሃ ጎቦ (ተራራ) የአሁኑ ጎብዮ ወይም ጎባ (Goba) የሚባለው ቦታ ነው፡፡ ጎብዮ ጎቦ ወይም ተራራ ከሚልው የትግርኛ ቃል የመጣ ነው፡፡




Map of early seventeenth Tigray showing the places mentioned by Barradas

*ካርታ 4. የትግራይ ግዛት በ16 ክፍለዘመን ካርታ: The Institute of Development and Education for Africa (IDEA)*

**ትግራይ አሁን ካላት የቆዳ መጠነ ስፋት በዚያን ግዜ በአራት እጥፍ ይበልጥ ነበር፡፡ ላይ የተጠቀሰው የታርክ ፀሃፊ ባራዳስ የፖርቹጋል የልኡካን መሪ በዚያን ጊዜ የነበረ የትግራይ ስፋትና ካርታ ወሰንና መዳረሻዎች በእንግሊዘኛ እንዲህ አስቀምጦት ነበር፡-**

"Among all the kingdoms that the Emperor of Ethiopia possesses today one of the greatest and most important is the Kingdom of Tygre. From north to south, that is from the limits of the Amacens [ሓማሴን ] to Enderta, it covers an area of from ninety to one hundred leagues; and from east, which is beside Dancali [ዓፋር], located at the entrance to the southern end of the Red Sea, to the west, bounded by the Tacasse [ተከዘ ] River beside the Semen, it covers an area of similar size, so that the kingdom has a nearly circular shape; unless we wish to extend it, some maintain should be done, as far as Lamalmon mountain range [ሊማሊሞ ተራራ]….

Degezmati (Dejazmach) Gelawdewos of Shire ruled over Wolkait and Seraye (now in Eritrea) during the early 17$^{th}$century. What this shows is that territorial polities sometimes could expand and sometimes could shrink, and yet even when Ethiopia was divided among the regional lords during the Era of Princes (1769-1855), one powerful prince by the name Ras Michael-Suhul, a Tigrayan, ruled over Tigray and Gondar from his court at Gondar and not from Tigray. Almost at the end of the Era of Princes, when Dejach Wubie ruled of Tigray, Tedla Hailu was appointed as governor of Wolkait-Tsegede, and some local historians (depending on oral

tradition/history), stretch back to the reign of Emperor Iyasu I (1682-1706), and tell us that Degezmati (Dejazmach) Naizghi was governing over Wolkait from Addi Remets until he was defeated in an ensuing skirmish by Dejazmach Mammo (Prof. Gelawdewos, 2016).

### 4.3. ከአፄ ምኒልክ በፊት የትግራይ ጥንታዊ ግዛቶች እና ወሰን በውጭ ጸሐፊዎች ዕይታ፣

#### 4.3.1. <u>የትግራይ ጥንታዊ ግዛቶች በሬቨሬድ ሚካኤል ሩሴል፣</u>

ከ150 ዓመት በፊት  በሩሴል 1833 ዓ.ም የተፃፈ መፅሃፍ እንደሚያስረዳው የትግራይ ክልል ተከዘ ማዶ ያሉትን በምዕራብ ወልቃይትና ወገራ እስከ ሰሜን ተራሮች ዋልድባን ጨምሮ እንደሆኑ ይህንን መጽሐፍ ያስረዳል፡፡ በደቡብ ደግሞ ኦፍላና ላስታን ጨምሮ እስከ ቆላ ማለትም አለማጣና ቆቦ አካበቢ እንደሚደርስ ይጠቅሳል፡፡ በጠቅላላ ታች እንደተመለከተው የትግራይ ጥንታዊ ግዛቶች መሃል ላይ ያሉ ትግርኛ ተናጋሪ (አክሱምና አድዋ) ጨምሮ ዓጋመ፣ እንደርታ፣ ወጀራት፣ ኦፍላ (ወፍላ)፣ ላስታ (አገውና ላሊበላ)፣ አበርገለ፣ ሰሜን ተራሮች እስከ ደባርቅና ዳባት፣ ወገራ (ፀገዴ)፣ ዋልድባ፣ ወልቃይት እስከ ሻንቅላ ድንበር ማለትም እስከ መተማ ያካትት ነበር፡፡ ይህንን ጥንታዊ የትግራይ ግዛቶች ከጎንደር በአማካይ እስከ 50 ኪ/ሜ ወጣ ብሎ ሙሉ በሙሉ እንደሚያጠቃልል ያመላክታል፡፡ በዚህ ፀሃፊ አገላለፅ አገው ላሊበላ ወይም ላስታ ከአክሱም ዘመነ መንግስት ጀምሮ ከትግራይ ጋር አልፎ አለፎ ቢሆንም በግዛትም በአስተዳደርም ይጠመሩ እንደነበር ያንፀባርቃል፡፡ ሌላው ይህንን የሩሴል መፅሃፍ ልዩ የሚያደርገው አማርኛ ተነጋሪ ህዝቦችም ለመጀመሪያ ግዜ የት አካባቢ እንደሚገኙና እንደሚኖሩ በግልፅ ያሰቀመጠ መፅሃፍ ነው፡፡ የአማርኛ ተነጋሪ እና የትግርኛ ተጋሪ ህዝቦች ድንበርም በትክክልና በግልፅ ያስቀመጠ መፅሃፍ ነው፡፡ ከዚህ መፅሃፍ በኋላ የተፃፉ የእንግሊዝኛና አማርኛ መጻሕፍት ማስረጃዎች አፄ ምኒልክ ወደ ስልጣን ከመጡና የአስተዳርና ግዛት ማስፋፋት ካደረጉ በኋላ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የአማራ ልሂቃን የወልቃይትና የተወሰኑ የራያ ወረዳዎች የወሎና ጎንደር ነበሩ የሚሉት በአፄ ምኒልክና አፄ ሃይለስላሴ ዘመነ መንግስታት የተፃፉና የአስተዳደራቸው ማስረጃዎች በማጣቀስ ነው፡፡ ስለዚህ የሚያቀርቧቸው የማንነት ጥያቄዎች በዚህ መፅሃፍና ከላይ በቀረበው እንዲሁም ሌሎች ከታች በሚቀርቡ ማስረጃዎች ዋጋ እንደሌላቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ መፅሃፍ ወገራ ወይም ወጀራት እያለ የሚያቀርበው ሁለቱም አንድ አካባቢ የሚገልፁ  ወይም ለተመሰሳሳይ ቦታ የተሰጠ ስም ሳይሆን ለተለያዩ ትግርኛ ተናገሪ ህዝብ መኖሪያ ቦታ ነው፡፡ ወገራ ከሰሜን ተራራ ቀጥሎ ያለው የፀገዴ እና አከባቢው መጠሪያ ስም ሲሆን ወጀራት ደግሞ በቀድሞ የእንደርታ አውራጃ አንድ ወረዳ

ሆኖ ከራያ ዓዘቦ የሚዋሰነውና ከራያ ህዝብ ተመሰሳሳይ የሆነ የቋንቋ ዘይቤ፣ ባህልና ልምድ ያለው ህዝብ ነው፡፡ ወፍላ/ኦፍላ (ኮረም) ለማለት ሲሆን አቨርግለ ደግሞ አበርገለ ማለት ነው፡፡ ሰሜን ደግሞ ከጎንደር ወደ ሰሜን እቅጣጫ ያለውን የሰሜን ተራራ ጨምሮ ደባርቕ፣ ዓዲአርቃይና ዳባት (እንዳባት) ወዘተ… የሚያጠቃልል ቦታ ነበር፡፡ ሁሉም ትግርኛ የሚናገር ህዝብ መኖሪያ ነበሩ፡፡ ይህን መፅሃፍ በእንግልዘኛ የተፃፈው በቀጥታ ሳይተረጎም እንዳለ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

**Boarder of Tigray (1833)**

The most important section of the empire is that which embraces the province of Tigre, bounded, as Mr. Salt informs us, on the north by the Bekla, Boja, Taku C", and several wild tribes of Shangalla; on the west by the mountains of Samen; and by the Denakil, Doba, and Galla territories. On the western side of the provinces now described are Sire, Samen, Wogara, which is sometimes called Wojjerat, Walkayt, and Waldubba. This last is occasionally extolled as one of the granaries of Abyssinia. The humid vales of Sire produce numerous palms and a variety of fruit-trees; enjoying, besides, all the beauty which arises from the vicinity of Tacazze, whose banks are covered with the most luxuriant verdure. Nor is Samen, which when viewed from a distance appears only as a series of mountain-chains, in any degree destitute of agricultural wealth. On the contrary, the table-land of Amba Gedion, which has so steep an ascent as to render it almost inaccessible, is said to be sufficient both in extent and fertility to support many thousands. Generally, the high range of the Samen hills, stretching from Waldubba to the south of Lasta, together with the line of the Tacazze, which flows in a north easterly course along its base, sufficiently point out the natural boundary between Tigre and Amhara (NUBIA AND ABYSSINIA page 74-75).

**<u>የአብሲኒያ ጥንታዊ ግዛቶች፣</u>**

Of these we shall have occasion to take some notice in the sequel; meantime we proceed to, give a tabular view of the Abyssinian provinces, which will serve much better than the minutest description to illustrate the distribution, the extent, and the relative position of the several parts of that great empire.

| I. AMHARA. | |
|---|---|
| 1. Amhara Proper. | 5. Begemder. |
| 2. Dembea. | 6. Angote. |
| 3. Damot. | 7. Walaka. |
| 4. Gojam. | 8. Marrabet. |
| **II. TIGRE.** | |
| 1. Tigré Proper. | 7. Avergalé. |
| 2. Agamé. | 8. Samen. |
| 3. Enderta. | 9. Temben. |
| 4. Wojjerat, or Wogara. | 10. Siré, or Shiré |
| 5. Wofila. | 11. Walkayt. |
| 6. Lasta. | 12. Waldubba. |
| **II. MIDRE BAHARNAGASH, OR DISTRICT OF THE PRINCE OF THE SEA.** | |
| 1. Masuah. | 6. Amphila. |
| 2. Arkeeko. | 7. Madir. |
| 3. Weah. | 8. Arena. |
| 4. Zullo. | 9. Duroro. |
| 5. Tubbo. | 10. Jarvela. |
| **IV. INDEPENDENT STATES IN THE SOUTH.** | |
| 1. Shoa. | 7. Cambat. |
| 2. Efat. | 8. Hurrur. |
| 3. Gooderoo. | 9. Gidm. |
| 4. Enarea. | 10. Adel. |
| 5. Gurague. | 11. Bali. |
| 6. Kaffa. | 12. Dawaro. |

*ምንጭ: የአብሲንያና ኑቢያ ታሪክ 1833 ዓ.ም ሬቨሬድ ሚካኤል ሩሴል*

### 4.3.2. ጥንታዊ የትግራይ ግዛቶች በውጭ የታሪክ ሙሁራን፣ ዲፕሎማቶችና ፀሃፊዎች፣

የትግራይ ጥንታዊ ግዛቶችን በተመለከተ - አቶ ሓዱሽ ረዳ "የቆሰለ ታሪክ" "ታሪክና ትርክት በኢትዮጵያ" በሚል መጽሐፋቸው ከገፅ 312 እስከ 313 የዶናልድ ኤን ሌቪንን መፃሕፍቶችን በመጥቀስ እንዲህ አስቀምጠዉታል፡- ወልቃይት፣ ፀገደ እና ፀለምቲ ብቻ ሳይሆን፣ ኩታ ገጠም የሆነው ሰፋ ያለ የሰሜን ጎንደርና ደቡባዊ ምስራቅ የዋግ ግዛት የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝብ የመኖሪያ ክልል እንደሆነ wax and Gold (ሰምና ወርቅ) በተባለው መፅሐፋቸው ውስጠኛ ሽፋን ክፍል በጥናት የደረሱበትን የኢትዮጵያ ካርታ ላይ ሰርተው እንዳቀረቡት አስቀምጠዉታል፡፡ የካርታ ጉዳይ ከተነሳ ይላሉ አቶ ሓዱሽ ረዳ፣ ሳሙኤል ጎባት፣ገፎን ዶረሲና እና ዴቪድ ፍሊፕስንም የፀለምቲ፣ የወልቃይት፣ የፀገደ፣ ሁመራና እንዲሁም የደቡብ ትግራይ ራያና የኮረም አከባቢዎች በትግራይ ስር እንደነበሩና ትግርኛ ተናጋሪ መሆናቸውን ግልፅ በሆነ ቋንቋ ፅፈውና ስለው አድርሰውናል ሲሉ አስቀምጠዉታል፡፡ እነዚህ በአቶ ሓዱሽ ረዳ በብዛት የተገለፁት ወደ አስራ ሁለት የሚጠጉ በተለያዩ ጸሐፊያን እና ዲፕሎማቶች የተፃፉ ማስረጃዎች አራቱን መርጠን በድጋሚ እንዳለ አንባቢያን ግንዛቤ እንዲያገኙ አቅርበነዋል፡፡

**ሀ. አባ ፍራንሲስኮ አልቫሬዝ፣**

በ16ኛው ክፍለ ዘመን እ.ኤ.አ በ1520 ዶም ሮድሪጌዝ ደ. ሊማ የሚመራው የፖርቱጋል መንግስት የልዑካን ቡድን አባል ሆነው ወደ ኢትዮጵያ የገቡት አባ ፍራንሲስኮ ኤልቫሬዝ በሰሩት ካርታ ላይ ትግራይ የዛሬው ወልቃይት እስከ ሱዳን ጠረፍ ተከትሎ ከዶብዓ (ራያ) ቀጥሎም ከደንከል ጋር እንደሚገጥም ወደ መሃልና ነፋሻማው ግዛት ሲዞሩ አሁንም ከዶብዓ ጋር እንደሚዋሰን የዶብዓዎች ግዛት በምዕራብ እንዳመኾኒ፣ አላጀና ወጀራት ሆኖ እስከ ቀይ ባሕር ጠረፍ የሚደርስ መሆኑን፣ የደረሱበት በምዕራብ ሽረንና የአሁኑን ወልቃይትን ተሻግሮ ከግብፅ ግዛት (ደቡብ ግብፅ ወይም ኑብያ የአሁኑ ሱዳን ኢትዮጵያ በሚል ስም የሚካለል ሰለነበር) ጋር እንደሚዋሰን በደቡብ ጫፍ የምትገኘው የዶብዓ ግዛት በትግረ መኾኒ ስር የትግራይ አካል እንደሆነችና የትግራይ አዋሳኝም ዶብዓን (ራያን) አልፎ ከወሎ ሮቢት ምዕራብ ተራራውን አልፎ ላይ ቃሲም አጠገብ የዛሬው የላስታ ግዛት አንጎት ላይ እንደሚገናኝ አብራርተው ፅፈዋል፡፡

**ለ. አባ ማኑኤል ደ. አልመዳ፣**

የትግራይ አዋሳኝ ከሰሜን ከምፅዋና ሕርቂቆ (ሕርጊጎ) እስከ የዓጋመዋ ዱፋሎ ደቡብ (አንፈላ) የቀይ ባሕር ጠረፍ፣ በምስራቅ ቡር (ደንከል)፣ በደቡብ በዶብዓ ጫፍ ከላስታ ወሰን አንጎት ላይ ያለውን መስመር፣ በደቡብ ምዕራብ የስሜን ግዛት እንደሚዋሰን ገልፀዋል፡፡ የወገራ አውራጃ ሰሜናዊ ክፍል የትግራይ ግዛት እንደሆነና የለማልሞ የተራራ ሰንሰለት ፈላሻዎች የሰፈሩበት መሃል ወገራና ስሜንን ከትግራይ እንደሚካፈል አብራርተዋል፡፡ የለማልሞ ገደልን ሽቅብ ሲወጡ በዳጉሻ (ዳሸን ወይም ደጀና) ተራራ አናት ላይ ሲራራ ነጋዴዎች እረፍት የሚያደርጉባት ሸቀጣ ሸቀጥ የሚገበያዩባት ቀረጥ የሚከፈልባት መንደር ትገኛለች፡፡ የዚች መንደር ነዋሪዎች "ስዋ" እየጠመቁ ለነጋዴዎችና ለአላፊ መንገደኞች እንደሚሸጡም ጠቁመዋል፡፡ (ስዋ ትግርኛ ቃል ሲሆን በአማርኛ ጠላ ማለት ነው)፡፡ ይህም ነዋሪዎቹ ትግርኛ ተናገሪ ህዝቦች እንጂ ሌላ እንዳልሆኑ ይጠቁማል፡፡ እዚች የለማልሞ መንደር ላይ ሆኖ በምዕራብ፣ በሰሜንና በምስራቅ መላዋን የትግራይ ግዛት ማየትና የወገራን የስሜን አዋሳኞቹን መዳሰስ ይቻላል፡፡ በሌላ ዘገባቸው የፀለምቲ አውራጃ፣ የድበዓ (ራያ) የስለዋና የአበርገለ ግዛቶችን በትግራይ ክፍል ግዛቶች መሆናቸውም ጭምር ጠቅሰዋል፡፡

***ሐ. ረቨረንደ (ሊቁ ቄስ) ሳሙኤል ጎባት፣***

በማህበራዊ ጉዳዮች በተጨማሪ ከተወልን መረጃዎች አንዱ በትግራይ የሚገኙትን አክሱም፣ ደብረአባይ፣ ጉንዳጉንዶ፣ ደብረዳሞ፣ ዋልድባ ፍፁም ሰለማዊ ጦርነት የማይካሄድባቸው የወዳጅ ሆነ የጠላት መጠጊያና መጠለያ የሆኑ የሚከበሩና የሚፈሩ


ቅዱስ ስፍራዎች መሆናቸው ጠቅሰዋል፡፡ በተጨመሪም ዋልድባ፣ ወልቃይትና ፀገዴ በሰሜናዊ ምዕራብ ሲገኙ በትግራይ ርእሰ መኳንንት ስር ስለነበሩና ዓመታዊ ግብር ለትግራይ ፈሰስ ማድረግ ግዴታ እንደነበረባቸው መፅሃፋቸው ላይ አስፍረዋል፡፡ በመጨረሻም ቂስ ጎባት በመፅሐፋቸው ከተከዘ ወንዝ በምዕራብ በኩል ያለው ሰፊ ቦታ በምዕራብ ትግራይ አስተዳደራዊ ክልል ውስጥ እንደሆነ በጊዜው ባሰፈሩት የካርታ ማስረጃ ይገኛል፡፡

**መ. ፕሮፌሰር ዶናልድ ኤን ሊቪን፣**

እንደቀደምት ፀሃፊዎች ወይም ተጓገሮች በተፈጥሮ ሀብት በኢኮኖሚና ወታደራዊ ጉዳዮች ላይ ሳይሆን በተለይ በቋንቋ በህግና በባህል ስርዓት ላይ ያተኮረ ጥልቅ ጥናት አድርገዋል፡፡ ወልቃት፣ ፀገዴ፣ ቃፍታ፣ ሑመራ፣ ፀለምቲና ከፊል ዋግ የትግርኛ ተናጋሪ ህዝቦች የመኖሪያ ክልል መሆናቸው በጥናት ደርሰውበት፣ በመፅሐፋቸው ውስጥ በተቀመጠው ካርታ ላይ በግልፅ አመላክተዋል፡፡ እኝህ ፀሃፊ ታላቋ ኢትዮጵያ በሚለው መጽሐፋቸው በወቅቱ የደብረ ታቦር ትልቁ የገበያ ማእክል እንደነበረና ከጭልጋ፣ ከቅማንት፣ ከጋይንት፣ ከትግራይ፣ ከደሴና ከአፋር ከዝንጅብል እስከ ጨው የተለያዩ የሸቀጥ ዕቃዎች እየመጡ ገበያውን ይሞሉት እንደነበረ የዘገበ ሲሆን፣ በተለይ ከትግራይ (Cotton from Tigrean district of wolqaite- eleven days) ማለት የጥጥ ምርት አስራ አንድ ቀናት በሚፈጅ ጎዞ የትግራይ አውራጃ ከሆነችው ወልቃይት እንደሚገባ በመፅሐፋቸው ዘግበዉታል፡፡

## 4.4. ከአፄ ምኒልክ በፊት የትግራይ የግዛት ወሰን፣

አፄ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከመሆናቸው በፊት ትግራይ ተብሎ የሚታወቅ ግዛት በሰሜን የኤርትራ ቦታዎች ያካተተ የነበረ ሲሆን በደቡብ ደግሞ በወሎ (አይሎሃ) ኣለውሃ-ምላሽ በጎንደር ለማሊሞ እምባ ጊዮርግስ ድረስ የሚዘልቅ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ሆኖም ኤርትራን ሳይጨምር የትግራይ ካርታ ስፋቱ 114000 ስኴር ኪሎሜትር እንደነበር ከጎግል የተወሰደ ልኬት ያሳያል (ሀዳሴ ኢትዮጵያ, 2011)፡፡




*ካርታ 5. ቅድመ አፄ ምኒልክ የትግራይ የግዛት ወሰን (ከጫፍ ሁመራ እስከ አሰብ ድንበር)*

አፄ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ከሆኑ በኋላ ግን በምእራብ ትግራይ በኩል ያለውን ሰፊ መሬት ማለትም ዙርያው 807 ኪ.ሜ. የሆነው 25793 ስኴር ኪሎሜትር ስፋት ያለው የትግራይ ቦታ ቆርሶ ወደ ጎንደር ማካለሉ ታሪክ መዝግቦታል፡፡ እነዚህ ወደ ጎንደር የተወሰዱት ቦታዎች ወልቃይት፣ ፀገዴ፣ ሑመራ፣ ወገራ፣ ፀለምቲ፣ ደባርቅ፣ ዓዲ- አርቃይ፣ እምባጊዮርግስ ወይም ዳባት ምላሽ ያለውን መሬት ሳያጠቃልል ማለት ነው፡፡ ተቆርሶ የተወሰደው የአስተዳደር ወሰን በጎግል ካርታ ሲታይ እንደሚከተለው ይመስላል፡፡




*ካርታ 6. በአፄ ሚኒሊክ ተቆርሶ ወደ ጎንደር የተካለለው የትግራይ የግዛት ወሰን (የተወሰዱ የምዕራብ ትግራይ ቦታዎች ካርታ)*

የትግራይ ካርታ አፄ ምኒልክ 25.8 ሺ. ስኴር ኪ.ሜ. ቆርሶ ወደ ጎንደር ካካለለ በኋላ የነበረው የትግራይ ቅርፅ እንደሚከተለው ይመስል ነበር፡፡ ከስዕሉ እንደሚታየው አፄ ሚኒሊክ በሚያስተዳድሩት ኢትዮጵያ የትግራይ ግዛት በአማካይ 1388 ኪ.ሜ. ዙርያ ያለው 85378 ስኴር ኪሎሜትር ስፋት እንደነበረው ያሳያል፡፡

.




*ካርታ 7. በአፄ ምኒልክ ዘመን የትግራይ የግዛት ወሰን (የምዕራብ ትግራይ ቦታዎች ከተወሰዱ በኋላ ያለውን ካርታ ግን እስከ አሰብ ድንበር እና ራያ ቆቦ ያከተተ)*

### 4.5. በአፄ ምኒልክ የምዕራብ ትግራይ ግዛቶች መቼና እንዴት ወደ ጎንደር ተወሰዱ?

አፄ ዮሃንስ መጋቢት 2 1881 ዓ.ም መተማ ላይ ከተሰዉ በኋላ የሳቸው ዙፋን ለመውረስ በራስ መንገሻ ዮሃንስ፣ ራስ አሉላ ኣባነጋ እና ሌሎች የትግራይ መሳፍንት እና ንጉስ

ምኒልክ መካከል የስልጣን ሽኩቻ ሲደረጉ ነበር፡፡ ከብዙ ትግልና ሽኩቻ በኋላ የትግራይ መሳፍንት ሳይሳካላቸው ሲቀር ንጉስ ምኒልክ ጥቅምት 25 1882 ዓ.ም ንጉሰ ነገስት ተብለው ዘውድ ጫኑ፡፡ በመጨረሻም የትግራይ መሳፍትን እርቅ አውርደው በአፄ ምኒልክ ስር ለመተዳድር ሀሳብ ቀረበ፡፡ ግን በምኒልክ ስር ብቻ ለመተዳደር ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ አራት ቅጣቶች በመጀመሪያ እንዲተገበሩ ጫና እንደተደረገባቸው የታሪክ ተመራማሪው ኤርሊክ ሃጋይ በመጥቀስ (ፍኖተ ሰሜን, መፅሄት 2008 ዓ.ም) ገልፀዋል፡፡

1. በራስ ሓጎስ ሲተዳድር የነበረው የምዕራብ ትግራይ ፀለምቲ፣ ዓዲ አርቃይ፣ ደባርቕ እና ዋልደባን ጨምሮ ለንግስት ጣይቱ ርስት እንዲሆን የሚል፡፡ በዚህ ውሳኔ መሰረት ፀለምቲ ማለት ወልቃይትና ፀገደም ስለሚያጠቃልል ከፀለምቲ አንድ ላይ ወደ ጎንደር ተጠቃለሉ የሚሉ አሉ፡፡ ሆኖም ግን ይህ አባባል ትክክል አይደለም፡፡ ወልቃትና ፀገደ በኋላ በአፄ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት በ1942 እ.እ.አ (ደንብ ቁጥር/ Decree No.8) ውሳኔ መሰረት ነው የተወሰዱት:: ዝርዝር መረጃው ታች በ 5.2 ተገልፀዋል)፣
2. ንቡረኢድ እየተባለ ከድሮ ጀምሮ ለአክሱም አስተዳደሪ የሚሰጠው ሹመት ከቤተክህነት ወጥቶ ወይም ከአከባቢው ገዥ ወጥቶ በንጉስ ምኒልክ እንዲሆን፣
3. እንደርታ የነበረው ጉልት ለልዕልት ዘውድቱ እንዲሆን፣
4. ከትግራይ የሚሰበሰብው ግብር ወደ ንጉሰ ነገስት እንዲገባ፣

በዚህ ትእዛዝ መሰረት ለብዙ ዘመናት የትግራይ ወረዳዎች ወይም አካባቢዎች የነበሩት ማለትም ፀለምቲ፣ ዓዲ አርቃይ፣ ደባርቕ እና ዋልደባን ጨምሮ በቤጌምድር በኋላ በጎንደር ስር እንዲተዳደሩ ሆነ፡፡ እነዚህ የምዕራብ ትግራይ ወረዳዎች ከዚህ ግዜ ጀምረው እስከ ኢህአዴግ ወደ ስልጣን እስኪመጣ ድረስ የጎንደር ግዛት ሆነው ቆይተዋል፡፡ ህዝቡ በባህልም በቋንቋም ከማይመሳሰለው ህዝብና አስተዳደር መደመር ለመሬትና ግዛት ሲባል የተደረገ የግዛት ማስፋፋት ዘዴ ነበር፡፡ ወደ ጎንደር የሚጠጉትን ወረዳዎች የአምርኛን ቋንቋ በቀላሉ የለመዱት ሲሆን፣ የፀለምቲ ወረዳ ህዝብ ግን የትግርኛን ባህልና ቋንቋ ጠብቀው ቆይተዋል፡፡

### 4.6. በአፄ ኃይለስላሴ የተወሰዱ የትግራይ ግዛቶች፣

የትግራይ ህዝብ እላዩ ላይ ይደርስ የነበረውን አስከፊ ጭቆና በተናጠልም በቡድንም መልክ በመቃወም በዘውዳዊ ስርዓት ላይ ያነጣጠረ ህዝባዊ አመፅ በስፋት ይታይ የነበረ ቢሆንም፣ በተለይ በዘመነ ኃይለስላሴ በዓይነቱ ልዩ የሆነ ከደቡባዊ ትግራይ ጀምሮ እስከ

ምስራቃዊና ማእከላዊ ትግራይን ያዳረሰ ከፍተኛ የህዝብ መነሳሳትና ዓመፅ ፈጥሮ የዘውዳዊውን ስርዓት ከትግራይ ጠራርጎ ያወጣው ሲሆን የዘውዳዊው ስርዓት ከስረ-መሰረቱ ያናጋ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡ ይህን ማዕበል ተከትሎ የንጉስ ኃይለስላሴ ዘውዳዊ መንግስት ከፍተኛ አደጋ ላይ በመውደቁ፣ ከኢንግሊዝ መንግስት ድጋፍ በመጠየቅ የህዝቡን መነሳሳት በእንግሊዝ አውሮፕላን ከየመን እየተነሱ ባደረጉት አስነዋሪና አሰቃቂ ጭፍጨፋ የህዝቡ ዓመፅ ለጊዜው እንዲበርድ እና እንዲበተን አድርጎታል፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር የንጉሱ ድምዳሜ "<u>ትግሬ አንድ ላይ ከሆነ የተረጋጋ ስልጣን አይኖረንም፣ ስለዚህ የህዝቡ ተቃውሞ ለመቆጣጠር ከፋፍለን መግዛት ይኖርብናል</u>" የሚል ድምዳሜ ተደረሰ፡፡ በዚህ ድምዳሜ መሰረት የንጉስ ኃይለስላሴ መንግስት ልክ እንደ አፄ ምኒልክ በወልቃይት ያደረጉት፣ የተወሰነ የራያ አከባቢ ወደ ወሎ በማካለል የትግራይ ህዝብ በሶስት ቦታ (በጎንደር፣ በወሎ እና በትግራይ) እንዲከፋፈል ተደርጓል (ህዳሴ ኢትዮጵያ 2011)፡፡

ይህንንም የትግራይን መሬት/ግዛት ከምዕራብና ከደቡብ ቆርሶ በመውሰድ የህዝቡ ቁጥር መቀነስ እና በኢኮኖሚ ማዳከም ነበር (ዮሴፍ ገብረህወት ከTMH ጋር መጋቢት 16 ቀን 2014 ዓም)፡፡ ይህንን የትግራይ መሬት ወረራ ወይም ማስፋፋት ዓላማና ህዝቡ በኢኮኖሚ ለማዳከም አፄ ኃይለስላሴ ሁለት አዋጆችን በማውጣት አወጁ፡፡ እነሱም፡-

1. ዶ/ር ሰለሞን ዕንቋይ Tigrai the Agony and the Ecstasy (2007) በሚል መፅሐፋቸው በገፅ 35 Schwab የተባለውን ፀሐፊ ጠቅሰው (Schwab, Peter (1979) Haile Selassie I Ethiopia's Lion of Judah)- Tigrai had already lost Welkait, Tsegede and all areas west of the Tekeze to Gondar in a new decree, the Decree No.8 of 1942 (Schwab,1979), which defined the provincial boundries. It also lost Agew Midir and Raya-Kobo to wollo in 1951 under the pretext of administrative and judicial efficiency.
2. ሓዱሽ ረዳ (የቆሰለ ታሪክ) ታሪክና ትርክት በኢትዮጵያ (2011) ገፅ 340 ከ1920-1926 ዓ/ም ራስ ስዩም መንገሻ ዋና ከተማቸውን ዓድዋ አድርገው ፀለምቲን ከወልቃይት-ፀገደ ነጥለው እና ከትግራይ ቀላቅለው ገዝቷል፡፡ ወልቃይት ፀገደ ደግሞ በደጃዝማች አያሌው ብሩ እንዲያዝ ተደርጓል፡፡ ይህንን ያደረጉት ራስ ተፈሪ መኮነን አልጋ ወራሽ ሆነው ተሾመው ያደረጉት ነው ይላል፡፡

እነዚህ ማሰረጃዎች የቀሩት የምዕራብ ትግራይ ወረዳዎች ማለትም ወልቃት፣ ፀገዴና ሑመራ በአፄ ምኒልክ ሳይሆን በአፄ ኃይለስላሴ ውሳኔ በ1942 እ.ኤ.አ በደንብ ቁጥር 8 ከትግራይ ወደ ጎንደር እንደተጠቃለሉ ያስረዳሉ፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪም የደቡብ ትግራይ

ሶስት ወረዳዎች (ራያ ቆቦ፣ ራያ አለማጣና ኦፍላ) እና የአገው ምድር በ1951 እ.ኤ.አ **በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን** ከትግራይ ተቆርሰው ወደ ወሎ ጠቅላይ ግዛት እንዲጠቃለሉ ተደረገ፡፡ የትግራይ ድንበር ወይም ግዛት በደቡብ እስከ 1948 ዓ.ም ድረስ እስከ አለውሃ ምላሽ እንደነበረ የሰውና የፅሁፍ ማስረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ የደቡብ ትግራይ ድንበር መደረሻው በደቡብ አለውሃ (ጎቦ አለውሃ: በኋላ ጎቦ የሚለውን ጎብየ ወይም ጎባ Goba እየተባለ የሚጠራው) ሲሆን በደቡብ ምስራቅ ጎቦ ዞብል አሁን የዞብል ኮረብታ ድረስ የተዘረጋ ነበር፡፡ በወልድያ በኩል አለውሃ ሲደርሱ እንኳን ወደ ትግራይ ጠቅላይ ግዛት በደህና መጡ የሚል ታፔላ ወይም ምልክት እስከ 1948 ዓ/ም የነበረ ሲሆን ዞበል አካበቢ ደግሞ የአፄ ዮሐንስ ቤተመንግሰት ወይም ማረፍያ ተሰርቶ እንደ ነበር የአካበቢው የዕድሜ ባለፀጋ ሰዎችና በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን የወቅቱ የትግራይ ፓርላማ ተወካይ ፊውተራሪ ሙኡዝ በየነ ለድምፅ ወያነ በአንድ ወቅት ገልፀው ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የተደረገው ማካለል እስከ ደርግ ስርዓት የቀጠለ ሲሆን ካርታውም እንደሚከተለው ይመስል ነበር፡-




*<u>ካርታ 8. በአፄ ኃይለስላሴ እና በደርግ ዘመን የትግራይ የግዛት ወሰን(ከ1948 ዓ/ም በኋላ)</u>*

በትግራይ የቀዳማይ ወያነ አመፅ ሲነሳ በእንግሊዝ መንግስት አውሮፕላኖች በመደብደብ አመፁ ለማስቆም የተቻለ ሲሆን ከዛ ጊዜ ጀምሮ የትግራይ ህዝብ በሶስት ቦታ መክፈል ብቻ ሳይሆን፣ የተቀረው ትግራይ ተረጋግቶ እንዳይኖር እና ሌላ ተጨማሪ ዓመፅ እንዳያስነሳ በማለት የትግራይ ገዢዎችን እርስ በርሳቸው ማጣላት፣ ህዝቡ በአውራጃ እየተከፋፈለ እንዲናቆር ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከታች ያለው ስዕል እስከ ደርግ ውድቀት ጊዜ የነበረ የትግራይ ግዛት ክልል ሲሆን ዙርያው 1262 ኪ.ሜ. ሆኖ ስፋቱ ደግሞ 61054 ስኴር ኪሎሜትር የምዕራብ ትግራይ እና በደቡብም ትግራይም ኦፍላ እና አላማጣ ሳያካትት የትግራይ ግዛት የተወሰኑ የአፋር ወረዳዎች ዳሎል፣ ኤሬብቲ፣ አፍዴራ፣ ሰርዶ፣ ሽከት (አብዓላ)፣ በራሕለ፣ ጉጉብዶ (ያሎ) ወዘተ… ጨምሮ እስከ አሰብ ድንበር ነበር፡፡




*ካርታ 9. ከቀዳማይ ወያነ በኋላ እስከ የደርግ ስርዓት መውደቅ ጊዜ የነበረ የትግራይ ካርታ እና የቆዳ ስፋት የሚያሳይ ምስል*

ከታች እንደሚታየው በቀዳማይ ወያነ የህዝብ ዓመፅ በመነሳቱ ምክንያት ህዝቡን ከፋፍሎ ለመግዛት በማሰብ 980 ኪሎሜትር ዙርያ ያለው ስፋቱ 25261 ስኴር ኪሎሜትር ወይም 30% ከነበረው የትግራይ ቦታ በመቁረስ ወደ ወሎ እና ጎንደር እንዲካተት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት እስከ የደርግ ስርዓት መገርሰስ ድረስ የትግራይ የቆዳ ስፋት 61054 ስኴር ኪሎሜትር ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህ ማለት በጎንደር አዋሳኝ ከተከዜ ወንዝ ምላሽ ሲሆን ከወሎ ደግሞ ከማይጨው አከባቢ ከምትገኝ የመስዋእት ወይም ችንኮ-ማጆ የሚባል አከባቢ ሆኖ የአፋር ቦታዎች እንዳሉ በማካለል እስከ ኤርትራ ድንበር ነበር የተካለለው፡፡




*ካርታ 10. በአፄ ሃ/ስላሴ ተቆርሶ ወደ ወሎ የተወሰደ የትግራይ የግዛት ወሰን*

**ከነዚህ ማስረጃዎች እንደምንረዳው ትግራይን ለማዳካም በአፄ ምኒሊክና አፄ ኃይለስላሴ በተለያዩ ወቀቶች የተወሰዱ እርምጃዎች የትግራይ ጥንታዊ ግዛቶች በመቀነስ ህዝቡ በኢኮኖሚና አልፎም የህዝብ ቁጥሩ እንዲቀንስ ለበርካታ ዓመታት ተሰርቶበታል፡፡ በአጠቃላይ በሁለቱም መንግስታት ከትግራይ ተቀንሰው ወደ ወሎ እና ጎንደር የተወሰዱት ቦታዎች ይህንን ይመስላል፡፡**




*ካርታ 11. በተለያዩ ወቅት የሸዋ ነገስታት ከትግራይ የወሰድዋቸው ግዛቶች (ምንጭ ገብረየሱስ ረዳ, 2014 ዓ.ም)*

## 4.7. ወደ ወሎ የተጠቃለሉትን የአካቢው ህዝብ (ተጋሩ) ተቃውሞና የፅሁፍ ማስረጃዎች፣

እነዚህ ወደ ወሎ የተጠቃለሉት ወረዳዎች ማለትም የራያቆቦ፣ ራያአላማጣና ወፍላ (ኮረም) ወረዳ ነዋሪዎች ከትግራይ ተነጥለው ወደ ወሎ መጠቃለላቸው በፅኑ የተቃወሙ ሲሆን በተለይ ኮሚቴዎች በማቋቋም አስከ  አዲስ አባባ ድረስ በመሄድ ለንጉሱ ተቃውሚቸውን በግልፅ አቅርበዋል፡፡ የትግራይ ጠቅላይ ግዛት የነበሩትና ወደ ወሎ ከተጠቃለሉት የራያና ቆቦ አውራጃ አስተዳደሪ ሆነው በተሸሙት ደጃዝማች ደስታ ሽዋ ርካብህ የተነሳው የህዝብ ተቃውሞ ለወሎ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ የነበሩት ደጃዝማች ደምሴ ወልደ አማኑኤል የሁኔታው አሳሳቢነት ክትትል እንደሚያስፈልገው ከታች በማስረጃው ዳብዳቤ እንደተገለፀ በግልፅ ተቀምጠዋል፡፡ በህዝብ ተወክለው ወደ ወሎ አንሄድም የሚሉ ኮሚቴዎች የተሰጣቸው መልስ ግን ልክ እንደ አሁኑ ግዜ የትግራይ ጠቅላይ ግዛት ፖለቲካ እጅ አለበት በማለት ሰዎቹ ማለትም ኮሚቴዎቹ በትግራዋይነቻው እንዲታሰሩ፣ እንዲሰደዱ እና እንዲገደሉ ተደርገዋል (የማነ ገብረመስቀል, ገፅ 268)፡፡

እነዚህ ሶስት ወረዳዎች ትግርኛ ተናጋሪ ህዝቦች ነበሩ፡፡ አሁንም ናቸው፡፡ አልፎ አልፎ ወጣቱ ትውልድ በራያ ቆቦ አማርኛ ይናገራል እንጂ ስረ መሰረታቸው ተጋሩ ነበሩ፡፡ ይህንንም በግልፅ በኢህአዴግ 1983 ዓ/ም ክልል ሲፈጠር ከራያ አላማጣ መለየት የለብንምን ወደ ትግራይ አንድላይ መጠቃለል አለብን የሚል ጥያቄ አቅርበው ነበር፡፡ የራያ አለማጣና ኦፍላ ወይም ኮረም ህዝብ 98% ትግርኛ ተናገሪ መሆኑን ምንም የማያጠራጥር ሲሆን ከታሪክ መረጃም አልፎ እኛም በአካል እናውቀዋለንና፡፡ በአፄ ሃይለስላሴ የራያ አለማጣና ኦፍላ ትግርኛ ተናገሪ ህዝብ ወደ ወሎ መጠቃለል ያስነሳው ተቃውሞና በወቅቱ የነበሩት የወሎ ሹማምንት የተንፀባረቀው ስሜትና መልስ ታች የተፃፈውን ደብዳቤ ለታሪክ ማስረጃነት ተቀምጠዋል፡፡

ማስረጃ 2. የትግራይ ህዝብ ተቃውሞ ወደ ወሎ ግዛት መጠቃለላቸው



ቀዳማይ ወያነ 268

ማስታወቂ

ለክቡር ደጃዝማች ደሙበወልደ አማኑኤል

የወሎ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ

የራያና ቆቦ አውራጃ ግዛት ከሁን ቀደም በትግሬ ጠቅላይ ግዛት እንደሚተዳደረው ወደ ወሎ ጠቅላይ ግዛት መሆኑ ቀርቶ እንደተዛወረ ወደ ትግሬ ጠቅላይ ግዛት ብትሆኑ ይሻላል በማለት በልዩ ልዩ በበኩትና ለሕዝቡ የመሰብሰቢያ በቂ ገንዘብ በመላክ ሙስሊሞችና ፖሊቲካ ተደርጎ እኛም የሚሻለን የትግሬ ጠቅላይ ግዛት አስተዳደር ነው በማለት መከንያት እየፈጠሩና ፖሊቲካ በመንዛት እንዲሁም ከትግሬ ጠቅላይ ግዛት በምስጢር አ የተሰሩ ያውራጃውን ግዛት ፀጥታ ለማታወክ የተነሱ :—

1ኛ— አቶ ዓለሙረው ጉግሣ የአላማጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ዳኛ

2ኛ— ገራ ሙብራ በላይ የቀኛ ም/ወረዳ ገዥ

3ኛ— ቀኛ/ኃይሌ አጄት የአላማጣ ወረዳ ግዛት ቀና ፀሐፊ

4ኛ— ፊታ/ሕበቂ አባበር .. ም/.. ገዥ በ-ላበት

5ኛ— ..በሪንቶ አባበር .. .. ..


6ኛ— አቶ ብርሃኑ ካሣ የሕግ ጠበቃ

እንዲሁም ደግሞ ከትግሬ ጠቅላይ ግዛት የፖሊቲካ ሥራ ማስኬጃ በቂ ገንዘብ በማከማቸት የሚላከውን የሚያቀርብና የሚያከፍል አቶ ተሾመ አረርሣ እንዚህ በመሆናቸው ለጊዜው እውቂ ፍሬ ነገሩን ተከታትዬና ጠብቄ ለመያዝ በመከታተልላይ ስሆን እነዚሁም ከዚህ በላይ የተመለከቱት የመንግሥት ሠራተኞችና የሃገር ሽማግሌዎች ሕዝቡን በፖሊቲካ እየበበዙ ይህ አውራጃ ግዛት እንደተዛወረው ወደ ክቡር የትግሬ ጠቅላይ ግዛት ቢዛወር በምንም ዓይነት ልትጠየቁ አይገባም የማለትን በበኩት በማቀዱ ሕዝቡን ስለሰበሰቡትና እንዲሁም በፖሊቲካው ውስጥ የዚሁ ግዛት የአድሚኒስትሬሺዮን ከፍል ሃላፊ ሽማግሌዎች ይህን ሃሣብ ገደረዶች በመሆን እንደሰታወቀባቸው ከላይ በስማቸው ከተጠቀሱት ሰዎች ጋር የቃል ገንኙነት አያደረጉ ቢሆን ይሁን ባይሆን ይቅር በማለት ሃሣብ ለሃሣብ እ የተገባቡ መከነገሩ ውስጥ መኖራቸውን ተከታትያለሁ ይሁን እንጂ በነሱም በኩል ሁኔታቸውን በመለከት በዚሁ ፖሊቲካ በመገለፀራቸው የመንግሥት ሥራ ተከናውና ሰሥራ አልተቻለም :—

በለዚህ አሁን ለክቡርነትዎ ለጉዳዩ መነሻ ይህን ሃሣብ ብገልጽም በነሱ በኩል የተሾመረውን ሃሣብ ቸውን በፍጥነት ተከታትዬ ውጤቱን በቅርብ ከነማስረጃው አቀርባለሁ ነገር ግን አስከዚያ ድረስ ጉዳዩ ክቡርነትዎ እውቀው ይህ ሐሣብ ፖሊቲካ ከመነሻው ሌሎች የቻለበትን ተረድተውት በበኩልያ ነገሩን አስበው እንዲጠባበቁት ስል በማክበር ማስታወቂዬን አቀርባለሁ፤ ሌ.ኮማ

ሌላ የፅሁፍ ማስረጃ እንደሚያመለክተው ደግሞ የቆቦ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በአለማጣ ስር ሆኖ ግብር እየሰበሰበ ወደ ትግራይ ዋና ከተማ መቐለ እያስገባ እንደነበረ ማስረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህንን ታች ካለው በመቐለ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የተገኘውን የ1945 ዓ/ም የማዘጋጃ ቤት ደረሰኝ መመልከት ይቻላል::

<u>ማስረጃ 3. የራያና ቆቦ ማዘጋጃ ቤት ለትግራይ ጠቅላይ ግዛት ግብር ሲሰበስብ</u>


ሴሪ ፩ኛ

№ 02764

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት

በትግሬ ጠቅላይ ግዛት

የመቀሌ ማዘጋጃ ቤት

የማዘጋጃ ቤት ደረሰኝ ።

ከ [illegible]

ምክንያት [illegible]

በአኃዝ (55) ብር ፡ ሳንቲም

በፊደል [illegible] ብር

ከ — ሳንቲም ተቀብያለሁ ። [illegible] ቀን ፲፱፻[illegible] ዓ. ም.

[illegible] ፊርማ

**ምንጭ**: በፌስ ቡክ በ2008 ዓ/ም ሲዘዋወር የተገኘ


## 4.8. በዘመነ ደርግ የትግርኛ ተናጋሪ ህዝብ አሰፋፈር፣

### 4.8.1. የምዕራብ ትግራይ ህዝብ ወልቃይት፣ ፀገዴ፣ ሑመራና ፀለምቲ ትግርኛ ተናገሪ ነውን?

መልሱ አዎን ነው፡፡ ምክንያቱም የደርግ መንግስት በኢትዮጵያ ያሉ ብሄር ብሄረሰቦች አሰፋፈር ቋንቋ መሰረት በማድረግ በ1971 ዓ.ም በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ኢንስቲትዩት አጥንቶ ነበር፡፡ ይህ ካርታ በ1971ዓ.ም የታተመና ቋንቋን መሰረት ያደረገ የወቅቱ የሰሜን ኢትዮጵያ ብሔረሰቦች አሰፋፈር የሚያሳይ ነበር፡፡ ከታች በስእሉ እንደተመለከተው ትግርኛ ተናገሪ ህዝብ የሰፈሩበት ቦታ በዚያን ግዜ በአራት ክፍለ ሀገሮች ማለትም በትግራይ፣ በኤርትራ በወሎ (ራያቆቦ፣ አለማጣና ኮረም) በጎንደር (ወልቃይት፣ ፀገዴ፣ ሑመራና ፀለምቲ) ወረዳዎች በሙሉ ትግርኛ ተናገሪ ህዝብ እንደሰፈረበት እና በተለያዩ ክፍለ ሃገሮችም ተበታትነው እንድሚኖሩ ጥናቱ ያስረዳል፡፡ ከዚሁ ጥናት በመነሳትና ነባራዊ ሁኔታዎችን (ቋንቋ፣ ባህል፣ ልምድ እና የህዝቦች መስተጋብር) መሰረት በማድረግ የኢህአዴግ መንግስት እነዚህ በተለያዩ ክፍላተ ሀገር ተበታትነው የነበሩ ትግርኛ ተነጋሪ ህዝብ ከኤርትራ በስተቀር በትግራይ ክልል እንዲጠቃለሉ አደረገ፡፡ ለምሳሌ <u>አፋር ክልል</u> ከትግራይ፣ ከወሎ፣ ሸዋና ሐረርጌ ክፍለሃገሮች በነበሩት አፋርኛ ተነጋሪዎች እንደተመሰረተ፣ <u>ሱማሌ ክልል</u> በሐረርጌ፣ ባሌ፣ አርሲ፣ ወዘተ… በነበሩ ሱማሌኛ ተነጋሪ ህዝብ እንደተመሰረተ፣ የኦሮሚያና አማራ ክልሎች ደግሞ ልክ እንደሌሎቹ ክልሎች ተመሳሳይ ቋንቋና ባህል ያላቸውን ህዝቦች አንድ ላይ በማምጣት በተመሳሳይ መንገድ እንደተመሰረተ ዓይነት ማለት ነው፡፡ ይህንን ማስረጃ በሆርን አፌርስ (horn affiars) ድህረ ገፅ በዝርዝር ቀርቦ ነበር፡፡

በዚሁ ታች ካላው ካርታና ጥናት መሰረት በያኔው ጎንደር ክፍለ ሀገር ሑመራ፣ ወልቃይት፣ ጸገደና ጸለምቲ ወረዳዎች (በቀይ የተከበበ) በወሎ ደግሞ የራያ ቆቦ፣ አላማጣና ኮረም አካባቢ በብዛት ትግርኛ ተናጋሪዎች መኖሪያ ወይም አካባቢ እንደሆኑ ካርታው ያሳያል፡፡ ካርታው የታተመው በደርግ መንግስት መሆኑና ስለ አካባቢው ህዝቦች ማንነት ትልቅ ማረጋገጫ ነው፡፡ እንዲሁም አሰፋፈሩ "ህወሓት አመጣሽ ነው" የሚባለው ትርክትም እርባና ቢስ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ስለሆነም በዚህ መለኪያ ዛሬ በወረዳዎቹ ውስጥ ዲሞግራፊ ተቀይሮ ከሆነ በትግራይ ተወላጆች ላይ የዘር ማጽዳት ተፈጽሟል ብሎ ለመውሰድ ያስችላል ብቻ ሳይሆን ዓይነተኛና ሁነኛ ማስጃ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም የ1987 የህዝብ ቆጠራ እንደሚያሳየው ከአራቱ ወረዳዎች ህዝብ ቁጥር ውስጥ (ወደ 300ሺ.ህ ነው) ትግራዋዮች ከ85% በላይ ሲሆኑ የአማራው ብዛት 10% አካባቢ ብቻ ነው፡፡ ይህ

በሆነበት ሁኔታ ዞኑን ከትግራዋዮች በመቀማትና እነሱን በማጽዳት የህዳጣን አስተዳደር ለመመስረት መሞከሩ ጊዜያዊ የጉልበተኞች ምኞታዊ ካርታ መሳል ካልሆነ በስተቀር ዘላቂ መፍትሄ አይሆንም፡፡





*<u>ካርታ 12. ከ1983 ዓም በፊት የትግራኛ ተናገሪ ህዝብ አሰፋፈር የደርግ መግስት ማስረጃ</u>*

## <u>4.8.2. ደርግ በጦርነት ወቅት ያጠናው ጥናት ስለ ወልቃይንትና ፀገደ ህዝብ ማንነት፣</u>

የደርግ መንግስት ከህወሃት ጋር ከ1967-1983 ዓ/ም ባለው ግዜ ለ17 ዓመታት የርስ በርስ ጦርነት እንዳካሄደ ይታወቃል፡፡ በዚህ ጊዜ ደርግ ህወሃት በትግራይ ውስጥ ድጋፍ አለው ብሎ ቢያስብም በሰሜን ጎንደር (ፀገደ፣ ወልቃይትና ሑመራ) ግን እንዴት ተቀባይነት እንዳገኘ ዝርዝር ጥናት እንድያካሂዱ በዚያ አካባቢ ለነበሩት የጦር መሪዎች ትእዛዝ አስተላለፈ፡፡ የጥናቱ ውጤትም ህወሓት በሰሜን ጎንደርና ወገራ አውራጃዎች ተቀባይነት ያገኘበት ምክንያት 75% ተመሳሳይ ትግርኛ ቋንቋ ተናገሪ፣ ተመሰሳይ ልምድና ባህል እንዳላቸውና በተጨማሪም ከትግራይና ኤርትራ ህዝብ የሚዋሰን በመሆኑ ወያኔ ችግር

እንዳላጋጠመው የጀኔራሉ የጥናት ውጤት ያሳያል፡፡ ጥናቱ ሲያጠቃልልም ትግርኛ ተናጋሪና ተመሳሳይ ባህልና ልምድ ስላላቸው ወያኔ እዚያ አካባቢ ድጋፍ ለማግኘት ብዙም አልተቸገረም ይላል፡፡

*ማስረጃ 4. ደርግ ስለ ወልቃይት ህዝብ ያጠናው ጥናት ውጤት የመጀመሪያው ገፅ*


መ ግ ለ ጫ :-

1. ወ ሰ ተ :-

ሀ. የሕወሓት የወንበዴ ቡድን :-


በሰሜናዊ ምዕራብ ዕዝ ቁጥር ከሰለ [illegible] / 6 /
ዓይነት የወንበዴ ድርጅት የሚገኙ ሲሆን በተለይ በአ
ሁኑ ወቅት በክፍለ ሀገሩ ውስጥ ትልቅ ግፍ የሚፈፅ
ሙ የሕ.ወ.ሀ.ት የወንበዴ ቡድ ነው ::

— ለዚሁ የወንበዴ ወገን በተለይ የሰሜናዊ የወገራ አው
ራጃዎች ከትግራይና ከጎንደር ክፍለ ሀገራት ጋር የሚያ
ዋስኑ እንደመሆናቸው መጠን የትግሬው ሕዝብ [illegible] –
ተገርና ቋንቋ በመሆኑ ለወንበዴው ያለምንም ችግር –
ዘለቄ ለመግባት ጥሩ አጋጣሚ ሆኖለታል ::

— የሕወሓት የወንበዴ ቡድን ፀረ ሕዝብ ድርጊቱን ከማካሄዱም
በላይ ሌሎችን ፀረ ሕዝብ ቡድኖች ፤ ኢህዴን ፤ ኢህአፓን
ኢዲሀገና ወያኔዎችን በሚችለው ሁሉ እንዲመሰርቱለት –
ጥረት እያደረገ ነው ::

ም/ጀኔራል
/2084 አሥራት ብሩ
የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና
የሰሜናዊ ምዕራብ ዕዝ አዛዥ

*ማስረጃ 5. ደርግ ስለ ወልቃይት ህዝብ ያጠናው ጥናት ውጤት ሁለተኛው ገፅ*



<u>4.8.3. በ1994 (1987) ዓ/ም የተደረገ የህዝብ ቆጠራ ማስረጃ፣</u>

ከላይ ያሉትን 5.1. እና 5.2. ማስረጃዎች የሚጠናክረው ደግሞ በ1987 ዓ/ም የተካሄደው የኢትዮጵያ ስነ ህዝብና ቤቶች ቆጠራ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ የምዕራብ ትግራይ ወረዳዎች የነበሩት ላለፉት 40 ዓመታት በጎንደር ክፍለ ሃገር ተጠቃልለው የቆዩ ቢሆኑም ህዝቦቹ

የሚናገሩት ቋንቋ ግን ትግርኛ ብሂራቸውም ተጋሩ እንደነበሩ የ1987 ዓ/ም ስነ ህዝብና ቤቶች ቆጠራ መረጃ ያሳያል፡፡ የእነዚህ አካባቢ ህዝቦች ትግርኛ ተናገሪ መሆናቸው ቀደም ብሎ የሚታወቅ ቢሆንም በኢህአዴግ ግዜ አዲስ ክልል ሲመሰረት ግን ትግርኛ ተነጋሪ ብቻ መርጦ በትግራይ ክልል እንዳጠቃለለ እና ሌሎች በታሪክ የሚታወቁት አካባቢዎች ግን በሂደት በቋንቋቸውና በባህላቸው ወደ ሌላ ማለትም ወደ አማራ አልያም ወደ አፋር ስላደላ እንደተዋቸው በግልፅ ይታያል፡፡

**<u>ሰንጠረዥ 8. የምዕራብ ትግራይ ወረዳዎች 1987 ዓ/ም የህዝብ ቆጠራ ውጤት</u>**

| ወረዳ | ቃፍታ ሑመራ | ፀለምቲ | ወልቃይት | ፀገደ |
|---|---|---|---|---|
| ሁሉም ነዋሪ | 48,690 | 97,630 | 90,186 | 59,846 |
| ትግርኛ ተናጋሪ | 41,999 | 87,012 | 87,099 | 45,532 |
| አማርኛ ተናጋሪ | 3,800 | 10,382 | 2,734 | 14,226 |

**ምንጭ**:CSA1994 (1987 ዓም) የተደረገ የህዝብ ቆጠራ

<u>4.5.4. የወልቃትና ፀገደ የአካባቢ ስሞች፣</u>

በአፄ ምኒልክ ውሳኔ መሰረት የፀለምቲ አካባቢ፣ በአፄ ኃይለስላሴ ደግሞ ወልቃት፣ ፀገደና ሑመራ በቤጌምድር ስር ቢተዳደሩም በጣም የሚገርመው የአካባቢው ቦታዎች ልክ እንደ ህዝቡ ለ40 ዓመታት ቋንቋውን ወይም መጠሪያ ስሞቹን አልተቀየሩም፡፡ ለዚህ ምስክር ከዚህ ፅሑፍ አቅራቢዎች አንዱ ከ1986 ዓ/ም ጀምሮ እዚያው አካባቢ በመንግሰት ስራ ተመድቦ ሲሰራ ስለነበር ነው፡፡ በተጨማርም አቶ ገብረስላሴ አርአያ የተባሉ ጸሐፊ በ aigaforum እነዚህን የአካባቢ ስሞች ለጥፈው ነበር፡፡

በወልቃይት ውስጥ የሚገኙ የጣብያዎች/ቀበሌዎች/ቦታዎች ስም፡-

ዓዲ ሳግላ፣ ዕዳጋ ሰሉስ፣ ደለሳ ቆቓሕ፣ ሰላሳዓይና፣ ዓዲ ረመፅ ፣ ሩባ ሎሚ፣ ደብረ ማርያም፣ ታሕታይ ማይ ሑመር፣ ማይ ጋባ፣ ዓዲ ሰላም፣ ምድሪ ወይዘሮ ፣ መጉእ፣እንዳቦ፣ ብላምባ ቅርሺ፣ ፀብሪ፣ ዓወርቂ፣ ደጀና፣ ማይ ጥምቀት፣ ዓዲ ጋባ፣ ኩሊታ፣ ብላምባ ልቋስ፣ ብላምባ ሚቾአል፣ ወዘተ ..

ፀገዴ ውስጥ የሚገኙ የጣብያዎች/ቀበሌዎች/ቦታዎች ስም፡-

ከተማ ንጉስ፣ ዳንሻ፣ እንዳማርያም፣ እንዳስላሰ፣ ጨጓር፣ ማይ ዓጋም፣ ማይ ደልየ ፣ ዋልካ፣ ዳራ፣ ሒላብ፣ ኩዶ፣ መድሃኒኣለም፣ ዓዲ ባርጌራ፣ ደብሪ ሓርያ፣ እምባታሮ፣ እንጣኣቤላ፣ ወዘተ…

ሰንጠረዥ 9. የደቡበ ትግራይ ሁለት ወረዳዎች የ1987 ዓ/ም የህዝብ ቆጠራ ውጤት፣

| ወረዳ | ራያ አላማጣ | ኦፍላ | Key notes |
|---|---|---|---|
| ሁሉም ነዋሪ | 93,659 | 124,484 | The Tigrians are mainly engaged in smallholder agriculture, spate irrigation and dry season irrigation. Settlements are mainly along roads and iron roofed of the rural areas. Amharic is frequently used as trade language in towns. |
| ትግርኛ ተናጋሪ | 60,878 (64%), | 111,040 (89.2%), | |
| አማርኛ ተናጋሪ | 31, 844 (33%) | 4,307 (3.46%) | |
| አገው (Agaw Kamyr) | | 9,050 (7.27%) | |
| ሌሎች | 2,810 (3%) | 87 (0.07%) | |

**ምንጭ:** *Central Statistical Agency (CSA), 1987 E.C. (1994) national census report*

## 4.9. የኢትዮጵያ ግዛት አከላለል በተለያዩ መንግስታት እስከ ኢህአዴግ እውነታዎችና ስህተቶች፣

### 4.9.1. የኢትዮጵያ ግዛት አከላለል በተለያዩ መንግስታት፣


ህገመንግስቱ ከረቀቀ በኋላ፣ ከመፅደቁ በፊት ወደ ህዝቡ ወርዶ ነፃና ግልፅ ውይይት የተደረገበት ሲሆን በዚህ ላይ ከ18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ከ18 ሚልዮን በላይ ዜጎች በውይይቱ እንደተሳተፉ ሰነዶች ያሳያሉ፡፡ በዚህ መሰረት ህገመንግስቱ በርካታ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች የያዘ ሲሆን ከዚህ ፅሁፍ ዓላማ አኳያ

ግን ስለ የክልሎች አከላለል እና መብት የተቀመጡትን ነገሮች በማውሳት ከወልቃይት እና ራያ ጉዳይ በማያያዝ እናቀርባለን፡፡

ኢትዮጵያ አሁን የያዘችው የግዛት ወሰን በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ከጎሮቤቶቻችን ባዕድ ገዢዎቻቸው ጋር በተለምዶ በ1902 እና 1908 ስምምነት እየተባሉ የሚገለፁ ስምምነቶች መሰረት የተካለለ እና እስከ አሁን ድረስ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘ የግዛት ወሰን ነው፡፡ የአገር ውስጥ አከላለል ሲታይ ደግሞ የተለያዩ የአስተዳደር አከላለል የነበረ ሲሆን አንዴ በጠቅላይ ግዛት ሌላ ጊዜ በክፍለ ሀገር የሚታወቅ ነበር፡፡ በአፄ ምኒልክ እና በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት ይደረጉ የነበሩ አከላለል ሲታይ ለስርዓቱ በሚበጅ መንገድ ነበር፡፡ ለስርዓቱ በሚበጅ ሲባል ለስርዓቱ የአስተዳዳር እና የፀጥታ ጉዳዮች በሚመች፣ ለግብር አሰባሰብ በሚመች፣ የህዝብን ጥያቄ እና መነሳሳትን ለማፈን በሚያስችል ሁኔታ የሚደረግ ነው የነበረው፡፡ በየደረጃው የሚገኙ የአስተዳደር ቦታዎች ማለትም ጠቅላይ ግዛት፣ አውራጃ፣ ወረዳ እና ከዛ በታች የነበሩ የአስተዳደር እርከኖች ገዢዎች እና አስተዳዳሪዎች አሿሿም ደግሞ ለዚህ ዓላማቸው የሚጠቅምና ለስርዓቱ ያላቸውን ታማኝነት እየተመረጠ ነበር የሚሾመው፡፡

4.9.2. <u>አሁን ያለው የትግራይ ኣካላለል ከሕገ መንግስት አንፃር ሲታይ፣</u>

ህወሓት ለትጥቅ ትግል በረሀ ሲወጣ ብሄራዊ ጭቆና እንደ ዋነኛ ጥያቄ አድርጎ የተነሳ ሲሆን በዚያ ጊዜ የትግራይ ህዝብ ከብሄራዊ ጭቆና በማላቀቅ ከወንድም የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት ለመመስረት የሚል ዓላማ ይዞ ነበር የተነሳው፡፡ በዚህ ጊዜ የትግራይ ብሄራዊ ጭቆና ለማራገፍ ሲታገል <u>የትግራይ ድንበር ብሎ የወሰደው በታሪካዊ አመጣጡ ላይ ተመስርቶ 5 ብሄር የያዘ ማለትም ትግራይ ብሄር፣ አፋር ብሄር፣ አገው ብሄር፣ ሳሆ /ኢሮብ/ ብሄር እና ኩናማ ብሄር ያካተተ ነበር፡፡</u> በዚህ ጊዜ የነበረው ካርታ ሲታይ እንደሚከተለው ይመስላል፡-




*ካርታ 13. አምስቱ ብሄር ያጠቃለለ የትግራይ የግዛት ወሰን*

በዚህ መሰረት በህወሓት ስር ተጠልለው ይታገሉ የነበሩ ህዝቦች ሲታይ የትግርኛ ተናጋሪ ህዝቦች ብቻ ሳይሆኑ የአምስቱም ብሄር ህዝቦች ነበሩ፡፡ እንግዲያውስ ይህ ነበር የትግራይ ህዝብ የትግል መነሻ፡፡ ስለዚህ ህወሓት ደርግን ለመደምሰስ ብሎ ከተነሳበት ጊዜ ጀምሮ የወልቃይት፣ የራያ፣ የአፋር፣ የሳሆ /በዛን ጊዜ ሳሆ የአሁኑ ኢሮብ/ እንዲሁም የኩናማ ብሄር ህዝቦች በህወሓት ስር ታቅፈው እንደ ታጋይ፣ እንደ ሚሊሻ ሆኖው ከፍተኛ መስዋእት ከፍለዋል፡፡ ስለዚህ ነው የራያና የወልቃይት ህዝብ በህወሓት ስር ተደራጅቶ በምኒልክ እና በአፄ ኃይለስላሴ የተረገጠ ማንነታቸው እና ሳይወዱ ከብሄራቸው ተለይተው እንዲተዳደሩ የተደረገውን ለመመለስ ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍለዋል፡፡ ለዚህ ነው የራያና የወልቃይት ህዝብ በመራራ ትግሉ አሽቀንጥሮ የጣላቸው የትምክህት ኃይሎች አሁን ህይወት ዘርተው በአዲስ አበባ፣ ባህር ዳር እና በጎንደር መሽገው ስለ ራያና ወልቃይት ጠበቃ መስለው የሚታዩት፡፡

በህገመንግስቱ መሰረት አሁን ያለው የትግራይ የግዛት ወሰን አሁን ያለው አከላለል ታሪካዊ ይዞታ መሰረት ያደረገ ሳይሆን ህገመንግስቱ ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት የብሄር እና ቋንቋ እንዲሁም የአኗኗር ዘይቤ፣ ባህልና የህዝቦች ትስስር መሰረት በማድረግ የተካለለ ሲሆን፣ ህገመንግስቱ ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት ለመተግበር የሚያስቸግሩ እና አከራካሪ የሆኑ አከባቢዎች በህዝበ ውሳኔ ወይም ምርጫ እንዲካለል ተደርጓል፡፡ ለንፅፅር እንዲያመች ስዕሉ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡




*ካርታ 14. በህገመንግስቱ መሰረት የተካለለ የትግራይ ክልል ወሰን*

ከደርግ ውድቀት በኋላ ህገመንግስቱ ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት የተደረገው አካለል፣ የትግራይ ክልል የቆዳ ስፋት እና ዙሪያ ሲታይ እላይ በስእሉ እንደሚታየው ዙርያ 1485 ኪ.ሜ. ሲሆን ስፋቱ ደግሞ 53036 ስኴር ኪ.ሜ. ሆኖዋል፡፡

በህገ-መንግስቱ መስፈርት እና አሁን ያለው የትግራይ የአስተዳደር ወሰን መሰረት የትግራይ ታሪካዊ ካርታ እንደሚያሳየው 114000 ስኴር ኪሎሜትር ነው አሁን ያለው ግን 53 ሺ. ስኴር ኪ.ሜ. ነው ታድያ 61 ሺ. ስኴር ኪ.ሜ. ወይም 54% የትግራይ ግዛት የት ገባ? መጠየቅ ያለበት ጥያቄ ነው፡፡ አሁን ታሪካዊ አከላለል ብቻ እንደ መስፈርት በመውሰድ ትምክህተኞች በሚያነሱት የራያና የወልቃይት ጥያቄ መርሆ ተከትለን ስናየው፤ የትግራይ ክልል የመሬት ስፋት 114 ሺ. መሆን ነበረበት፡፡ አሁን ወደ ሌላ ክልል የተካለለው 61 ሺ. ስኴር ኪ.ሜ. ወደ ትግራይ መካለል የሚገባው ነበር፡፡ ልዩነቱ ነፍጠኞች የሚሉት የትግራይ ግዛት በደርግ የነበረ ብቻ መሆን አለበት ስለሚሉ ነው፡፡ ነገር ግን ህገመንግስቱ ባስቀመጠው መርሆ አሁን ያለው የትግራይ ካርታ ሲታይ ህወሓት ትግል ሲጀምር የነደፈው ሳይሆን ደርግ ከተደመሰሰ በኋላ ከኢትዮጵያ ህዝቦች በጋራ በመምከር የተደረሰ ስምምነት ነው ማለት ይቻላል፡፡ እንዴት? በሶስት መንገዶች

1. በህገመንግስቱ መሰረት የአፋር ብሄር ካለው የህዝብ ብዛት እና የቆዳ ስፋት ሲታይ እንደ ብሄር በአንድ ክልል መካለል ስለነበረበት በትግራይ ላይ የነበረው ሰፊ ቦታ ከብሄረሰቡ ጋር እንዲካለል ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት እታች ስዕሉ እንደሚታየው


1009 ኪ.ሜ. ዙርያ ያለው 43887 ስኴር ኪ.ሜ. ስፋት ያለው ቦታ ድሮ በታሪክ የትግራይ ተብሎ ከሚታወቀው በማስወጣት ወደ <u>አዲሱ የአፋር ክልል በመካለሉ፣</u>

2. ሌላው ምክንያት ደግሞ በትግራይ ታሪካዊ አመጣጥ በማእከላዊ ደቡብ ትግራይ ኣከባቢ ይኖሩ የነበሩ የትግራይ አገው ብሄር በብዛታቸው ኣኴያ ሲታይ በአማራ ውስጥ ያሉ የአገው ብሄር ህዝብ ስለሚበዙ የትግራይ ኣገው ወደ ኣማራ እንዲካለሉ ማድረግ ሁለተኛው ምክንያት ነው፣

3. ሶስተኛው ምክንያት ደግሞ በተለይ አይሎሁ-ምላሽ (አለውሃ) እና እምባ ጊዮርግስ-ምላሽ ሲታይ፣ ምንም እንኳ በታሪካዊ አመጣጡ የትግራይ ቦታ ቢሆንም ግን ደግሞ የህገመንግስቱ መርሆዎች ማለትም የቋንቋ፣ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ ሲታይ እነዚህ አከባቢዎች የተወሰነው ቦታ የአማራ ቋንቋ፣ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ በስፋት የሚስተወልባቸው ሲሆኑ ግሚሱ ደግሞ የትግራይ ቋንቋ፣ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ በስፋት ሲስተዋልባቸው እመሃል ላይ ደግሞ አጠራጣሪና የሁለቱም ብሄር (የአማራ እና የትግራይ) ቋንቋ፣ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ በስፋት የሚታይባቸው ነበሩ፡፡ በዚህ መሰረት የማያጠራጥሩ ቦታዎች ማለትም አማርኛ ተናጋሪ የሚበዛበት ወደ አማራ ክልል፣ ትግርኛ ተናጋሪ የሚበዛበት ቦታዎች ወደ ትግራይ ክልል ተካልለዋል፡፡ ለምሳሌ ከእምባ ጊዮርግስ እና ዓዲአርቃይ እስከ አይሎሁ-ምላሽ እስከ ቆቦ ወደ አማራ ሲካተቱ፣ ወልቃይት፣ ፀገደ፣ ሑመራ፣ ፀለምቲ፣ ኮረም፣ አላማጣ ወደ ትግራይ ተካልለዋል፡፡ በመሃል ላይ ለመለየት የሚያስቸግሩ አንዳንድ ቀበሌዎች እና ጎጦች ደግሞ የህዝብ ፍላጎት መሰረት በማድረግ ቀበሌና ከቀበሌ በታች በመውረድ የህዝብ ፍላጎት በመጠየቅ ድምፅ እንዲሰጥ ተደርጎ፡፡ በዚህ መሰረት ትግርኛ ተናጋሪ እያሉ በአብዛኛው ወደ አማራ በመምረጣቸው ወደ አማራ ክልል የተካለሉ አሉ፡፡ ለምሳሌ በአበርገለ አከባቢ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አማራ ተናጋሪ እያሉም ወደ ትግራይ በመምረጣቸው በትግራይ የተካተቱ አሉ፡፡ ይህ ሲደረግ ግን በታሪካዊ አመጣጥ ከአፄ ምኒልክ ዘመነ-መንግስት በፊት የትግራይ የነበረ ቦታ እንጂ የአማራ የነበረ ቦታ አንድም ወደ ትግራይ የመጣ አልነበረም፡፡

አሁን ያለው የአማራና የትግራይ ክልል የተፈጠረው በዚህ ህገመንግስት ባስቀመጠው መርሆ ተከትሎ የሁሉም ህዝቦች ይሁንታ ታክሎበት የተደረገ እንጂ በአንድ ወገን ወይም ቡድን የተሰራ ስራ አይደለም፡፡ ይህም የህወሓት አመራር፣ የብአዴን ኣመራር በደንብ የሚያውቁትና የተሳተፉበት ነበር፡፡ ማወቅ ብቻም ሳይሆን ከልቡ የሚያምንበት እና ለህዝበ ውሳኔ ብሎም ባለፉት 27 ዓመታት ይታገልለት የነበረ ጉዳይ ነው፡፡

አሁን ያለው የትግራይ ካርታ ከታሪካዊ ይዞታ ሲነፃፀር 54% የግዛት መሬት ወይም በ62184 ስኴር ኪ.ሜ. ያነሰ ነው፡፡ የዚህ ምክንያት ለህገመንግስቱ ተገዢ መሆንና ለዴሞክራሲያዊ አንድነት በማሰብ እንጂ ትምክህተኞች በሚያስቡት ቢሆን እማ 114000 ስኴ.ኪ.ሜ. በተደረገ ነበር፡፡ የትግራይ ህዝብ ለማንነቱ እና ለመብቱ ሲታገል የህዝቦችን መብት ለመንካት ሳይሆን የሌሎች ህዝቦች መብትም ልክ እንደ ራሱ መብት ለማክበርም ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም በሚከተለው ካርታ ላይ እንደሚታየው ስፋቱ 62.2 ሺ. ስኴር ኪ.ሜ. የሆነ፤ 2092 ኪሎሜትር ዙርያ ያለው የመሬት ወሰን፣ ምንም እንኳ በታሪካዊ አመጣጥ የትግራይ ቢሆንም፤ በህገመንግስቱ መስፈርት መሰረት፤ የአፋር እና የአገው ብሄር - በቋንቋ እና ብሄር መስፈርት፣ እንዲሁም ከእምባ ጊዮርግስ እስከ አይሎሃ ምላሽ ያለው አከላለል ደግሞ በህዝብ ፍላጎት መሰረት ወደ ሌላ ክልል እንዲካለል አድርጓል፡፡





*ካርታ 15. በህገመንግስቱ መሰረት ወደ ሌላ ክልል የተካለለ የትግራይ ታሪካዊ ወሰን*

እላይ ያለው ካርታ/ስዕል እንደሚያሳየው ከሆነ የትግራይ ህዝብ በከፍተኛ መስዋእትነት ብሄራዊ ማንነቱ እና መብቱ ካረጋገጠ በኋላ በታሪክ የሚያውቀውን 114000 ስኴር ኪሎሜትር ታሪካዊ ወሰኔ ይሰጠኝ አላለም፡፡ የታገለው ብሄራዊ ጭቆና እንዲወገድ እና ወሰን እና ማንነት በህዝቦች ፍላጎት እንዲወሰን ማድረግ ስለነበር፣ ትግራይ የኔ ይዞታ ነው የሚለው ታሪካዊ ቦታው ከአንድ መቶ ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ታሪክ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዚህ በርካታ የትውልዶች ዓመታት በርካታ ለውጦች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ በአጠራጣሪና አከራካሪ ቦታዎች የህዝቡ ውሳኔ እንዲታከልበት ተደርጓል፡፡




*ካርታ 16. በህዝቡ ቋንቋ፣ ባህል፣ የአኗኗር ዘይቤ እና ፍላጎት መሰረት ወደ አማራ ክልል የተካለለ የትግራይ ታሪካዊ ወሰን*

በዚህ መሰረት እላይ በካርታው የሚታየው በቀይ ቀለም የተከለለው ስፍራ በታሪክ ሲታይ የትግራይ ግዛት የነበረ ሲሆን በህገመንግስቱ አከላለል መሰረት የህዝቡ ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት፣ እንዲሁም የአገው ብሄር ህዝቦችም አብዛኛው በአማራ ክልል ስለሚገኙ በትግራይ ውስጥ ይገኙ የነበሩ የአገው ብሄር ህዝብ በአማራ ክልል ሆኖ በጋራ እንዲካለሉ ተደርጓል፡፡ አሁን የአሀዳዊ ስርዓት አቀንቃኞች ታሪካዊ የአስተዳደር አከላለል መሰረት በማድረግ በሚያነሱት ጥያቄ ይፈታ ከተባለ ይቅርና ወልቃይት እና ራያ ወደ አማራ ክልል ሊካለል አይሎሀ-ምላሽ፣ አገው ምድር ጨምሮ እስከ እምባ-ጊዮርግስ ወደ ትግራይ ክልል ነበር መካለል ያለበት፡፡ ነገር ግን ባለፉት 100 ዓመታት የነፍጠኛው ስርዓት ባደረገው ከፍተኛ የዘር እና የማንነት የማጥፋት እንቅስቃሴ እላይ በ1163 ኪሎሜትር ዙርያ እና በ18522 ስኴር ኪ.ሜ. ስፋት ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ምንም እንኳ በታሪክ የትግራይ ቢሆንም /አገው ሳይጨምር ለማለት ነው/፣ በስነ ልቦናም በመዋለድም በስደትም የአማራነት ማንነት እንዲወርሱ በመደረጉ የአከባቢው ነዋሪ በመካለሉ ጉዳይ ወደ አማራ ክልል በመምረጡ ህወሓት እና የትግራይ ህዝብ ምርጫውን በማክበር ተቀብለውታል፡፡




*ካርታ 17. በህዝቡ ቋንቋ፣ ባህል፣ የአኗኗር ዘይቤ እና ፍላጎት መሰረት ወደ አፋር ክልል የተካለለ የትግራይ ታሪካዊ ወሰን*

እላይ የሚታየው ካርታ ደግሞ ዙርያው 1009 ኪ.ሜ የሆነ፣ ስፋቱ 43.9 ሺ ስኴር ኪ.ሜ. የሆነ ቦታ ታሪካዊ አካለሉ የትግራይ ግዛት የነበረ ቢሆንም በዚህ አከባቢ የሚኖሩ ህዝቦች ማንነት ሲታይ ግን የአፋር ብሄር ማንነት ያላቸው በመሆኑ፣ የትግራይ ህዝብ የታገለለትንና ከወንድም የኢትዮጵያ ህዝቦች በጋራ ያፀደቀውን ህገመንግስታችን መሰረት በትግራይ ውስጥ ይተዳደሩ የነበሩ የአፋር ብሄር ህዝቦች በሌላ የኢትዮጵያ ክፍል ከሚገኙ የአፋር ማንነት ያላቸው ህዝቦች በጋራ የራሳቸው ክልል እንዲፈጥሩና የራሳቸው አስተዳደር እንዲኖራቸው ለማድረግ የአፋር ክልል እንዲመሰርቱ ተደርጓል፡፡
ይህ ስለ ትግራይ አከላለል መሰረት ኣድርገን ስለተነሳን እንጂ ይህ የአከላለል መርሆ በመላው አገሪቱ የተደረገ ሲሆን በህገመንግስቱ መሰረት 9 ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት እና 2 የከተማ አስተዳደር ተፈጥሯል፡፡ ይህን አከላለል ከተፈጠረ ጀምሮ የተወሰኑ አከባቢዎች ክልል መሆን ይገባናል፣ ወረዳ ወይም ልዩ ወረዳ መሆን ይገባናል፣ ቀበሌ መሆን ይገባናል ከሚሉ ውጪ መሰረታዊ የማንነት ጥያቄዎች ሳይቀርቡ ላለፉት 27 ዓመታት አገራችን ሰላምና መረጋጋት ሰፍኖባት ቆይቷል፡፡

4.9.3. <u>የትግራይ ግዛት አከላለልና በዘመነ ኢህአዴግ የተፈፀሙ ስህተቶች፣</u>

ህወሓት/ኢህአዴግ ወደ ሰልጣን ሲመጣ የኢትዮጵያ ካርታና ግዛት በታሪክ፣ ቋንቋ፣ ልምድ፣ ባህልና ማህበራዊ መስተጋብር መሰረት በማድረግ ያለፈውን የተዛባ ህዝቦችን የመከፋፈል አስተዳድር ለማስቀረት ሞክረዋል፡፡ ሆኖም ግን ከታሪክ አንፃር የትግራይ የነበሩት ሁሉም

ግዛቶች ለማስመለስ አልተሞከረም፡፡ አለፍ ብሎም ደርግ እስከወደቀበት ጊዜና ክልሎች እንደአዲስ እስከ ተዋቀሩበት ቅርብ ጊዜ ድረስ በትግራይ ካርታና አስተዳደር ስር የነበሩትን ወረዳዎች (ዳሎል፣ በራሕለ፣ ኩነባ፣ ሽኸት (አሁን ኣብዓላ)፣ መጋለ፣ ጉጉብዶ (አሁን ያሎ) እሬብቲ፣ ሰርዶ እስከ ጅቡቲና አሰብ ድንበር ያለውን) ወደ አፋር እንዲካለሉ መደረጉ በቋንቋ ምክንያት እውነትነት ቢኖረውም ኣብዛኛው ትግርኛ ተናገሪና በእርሻ የሚተዳድር ህዝብ የነበረውና ያለው የሽኸት (ኣብዓላና ህድሞ አካባቢዎች) ህዝብ ወደ አፋር መካለሉ ስህተት ነበር፡፡ በዚህ ብቻ ሳያበቃ ከአፋር ክልል ድንበር ሲካለልም ስህተት ተሰርተዋል፡፡ በንድፈ ሀሳብ የተስማሙት ደጋማ አከባቢዎች ወደ ትግራይ ቆላ ቆላውን  ደግሞ ወደ የአፋር ክልል ለማካለል ሲሆን በተግባር ግን የአፋር ክልል ወደ ደጋው በመውጣት ኬላቸውንና የክልሉን ባንዴራ በዴስአ ደን መሃል ሲሰፍሩ፣ በዓብላ (ሽኸት) በኩልም ወደ ደጋው የእንደርታ ቦታ ወጥተው ኬላቸው ሲተክሉ ነበር፡፡ ይህንን የደን ጭፍጨፋና ለተለያዩ የማሕበረሰብ ግጭት መነሻ ሆኖ ነበር፡፡ የትግራይ መንግስት ከ2013 ዓ/ም ግጭቱ በፊት ምንም መልስ አልሰጠበትም ወይም በጉልህ ሲቃወም አይታይም ነበር፡፡

ሌላው በአፄ ኃይለስላሴ ግዜ የተወሰደውን ራያ ቆቦ ደግሞ በአማራ ክልል እንዲሆን መፍቀዱ እውነትም ስሕተት ነበር፡፡ ምክንያቱም የራያ ቆቦ ህዝብ ከራያ አለማጣ ህዝብ በስጋ የተዛመደና የተዋለደ ሆኖ ሳለ ከቅርብ ጊዚያት ወዲህ ኣብዘኛቸው አማርኛ ቢናገሩም ወደ ወሎ ከመወሰዱ በፊት ግን አልፎ አልፎ ትግርኛ የሚችልና ሰነ ልቦናውምና ባህሉ ከትግርኛ ተነጋሪ አንድና ተመሰሳይ ነበር፡፡ በተለይ ደግሞ ወደ ትግራይ ክልል ለመካላል ፍለጎቱ ሃይለኛ ነበር፡፡ ግን ደግሞ በትግራይ በኩል ትኩረት አልተደረገበትም፡፡ ይህ በመሆኑ አብዛኛው ነዋሪው ህዝብ ከጊዜ ብዛት የተነሳ የአማራ ባህልና ስነ ልቦና ተላብሶ ይገኛል፡፡ በተመሳሰይ መልኩ የዋግ ህምራ እስከ ላሊበላ ያለው ከአማራ ይልቅ ስነልቦናውና ታሪኩም ጭምር ከትግራይ ይቀራረብ ነበር፡፡

ሌላው የህወሓት/ኢህዴግ ስህተት ታሪክ፣ ቋንቋ እና ባህልን መሰረት ያደረገ ክልል ለመፍጠር ያደረገው ጥረት በአማራ ክልል ተመተሳሳይ መንገድ አለመከተሉ ነው፡፡ ሐረሪን ክልል ያደረገ ህገ መንግስት አገዎችን ማለትም የአገው፣ ላስታና አዊ ህዝቦችን፣ የወሎ ኦሮሞዎችንና ቅማንቶችን ከአማርኛ ተናገሪ ህዝብ ጋር ተገቢ ባልሆነ መንገድ አንድ ላይ ማካለሉ ከፍተኛ ጥፋትና ስህተት ሰርተዋል፡፡ በበጎ ጎኑ የሚወሰደው ኣብዛኛው የአፋርኛ ተናገሪ ህዝብ ወደ አፋር ክልል እንድሄዱ ሲፈቅድ ለብዙ ዘመናት ትግርኛ ቋንቋቸው ጠብቀው የቆዩትን የወልቃትና ፀለምቲ ወረዳዎች ወደ ትግራይ ማካለሉ ጥሩ

ነበር፡፡ በአጠቃላይ የአካለሉ ሁኔታ ሲታይ ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ ስነ ልቦና እና የህዝብ ፍላጎት እንዲሁም ማሕበራዊ ትስስር መሰረት ያደረገና በጥልቀት የታየ መሆን ነበረበት፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግ ሲታይ ደግሞ ከትግራይና ትግርኛ ተናጋሪ ህዝብ ብዙ የሚመሳሰሉ በታሪክ አንድ የሚደርጋቸው ክስተቶች ሊታዩ ይችሉ ነበር፡፡ ለምሳሌ:- የአሸንዳ፣ ሻደይ እና ሶለል በዓል በአሁኗ ትግራይና ጥንታዊ ግዛቶቿ በሚገኙ ልጃገረዶች ተመሳሳይነት ባለው መልኩ ይከበራል፡፡ የሴቶች ፀጉር ሹረባ አሰራር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ከአክሱም እስከ ላሊበላ ያለውን የውቅር አብያተ ክርስትያናት መገለጫቸው ነው፡፡ ሌሎችም መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህንን ታሪክና ባህል ግምት ውስጥ ያስገባ አከላለል መፍጠር ይቻል ነበር፡፡

## 4.10. የአማራና ትግራይ ድንበር የሆነው የግጨው ጥያቄ እንዴት ተነሳና ተፈታ፣

የወልቃይትና የራያ ጉዳይ ወይም ጥያቄ አዲስ ክስተት አይደለም፡፡ አሁን ያለው የፌዴራል ስርዓት የማይዋጥላቸው የትምክህት ኃይሎች ሁሌም ሲያነሱት የነበረ ነገር ግን ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ብዙም እንደ ትልቅ አጀንዳ አይታይም ነበር፡፡ ምክንያቱ ህዝቡም አመራሩም በትክክል ይገነዘበው ስለነበር፡፡ ባለቤቶቹ (የራያና ወልቃይት ህዝቦች) ምንም ጥያቄ ሳይጠይቁ በጎንደር እና በባህርዳር ብሎም በአዲስ አበባ ሆኖ የማንነት የማይመለከታቸው ሰዎች ሲያነሱት ነበር ፡፡

ሆኖም ከላይ ካሉት ማስረጃዎች በመነሳት በታሪክ፣ በባህል እና ቋንቋ የወልቃይት ህዝብ ድሮም አሁንም ትግራዋይ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ይህንንም ህዝቡንም አከባቢውንም ይመሰክራሉ፡፡ ሆኖም የወልቃት ጥያቄ እንዴት ሊነሳ ቻለ የሚለውን ማየትና መዳሰስ ጠቃሚ ነው፡፡ በዋናነት የወልቃት ጥያቄ የተነሳው በወልቃይት ህዝብ ማለትም በፀገደ፣ ወልቃይትና ሑመራ ህዝብ ሳይሆን ጎንደር ማእከል ያደረጉ የሰሊጥ ነጋዴዎች ነበር፡፡ ጎንደር ከተማ መሽጎ ይህንን ጥያቄ አልፎ አልፎ ነጋዴዎቹ ሲያነሱት የነበረ ቢሆንም ተጠናክሮ የወጣው ግና የብአዴን ስውር እጅ ድጋፍ አግኝቶ ጥቂት የወልቃይት ተወላጆች ሕጋዊ ሽፋን በመጠቀም የወልቃይት ኮሚቴ በማቋቋም ነበር፡፡ ኮሚቴውም በህወሓት ታጋይ የነበሩት ኰሎኔል ደመቀ ዘውዱ ቡድን ከ 2008 ዓ/ም ጀምሮ ይመራ ነበር፡፡ ኰሎኔል ደመቀ ዘውዱ ወደዚህ የገቡት አምነውበት ሳይሆን በእልህና ቂም ነበር፡፡ ጡረታ ከወጡ በኋላ በንግድ ስራ ይተዳደሩ ነበር፡፡ በኋላም በእርሻ እንዲተዳደሩ ለአካባቢው አስተዳደር ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ ወድያውኑ 10 ሄክታር ለእርሻ የሚሆን መሬት

ይሰጣቸዋል፡፡ ኰሎኔል ደመቀ ዘውዱም *"ይህንን በቂ አይደለም፣ እኔ የአከባቢው ተወለጅ ነኝ፡፡ ከዚህም በላይ ይገባኛል ለሌሎች ሰዎች ግን ከዚህ በላይ ትሰጣላችሁ የሚል ጥያቄ ያቀርባሉ"፡፡* የአካባቢው አስተዳድር ደግሞ *"የእርሻ መሬት የሚሰጠው በአቅም እና ካፒታል እንጂ በፍላጎትና በአከባቢ ተወላጅነት አይደለም"* የሚል መልስ ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያትም አኮረፉ፡፡ በዚህ ቂም ተነስተው እና ከሰሊጥ ነጋዴዎችና ከሰሜን ጎንደር ብአዴን ፅሕፈት ቤት በተደረገላቸው ድጋፍ የወልቃይት አስመላሽ ኮሚቴ የሚል መሰረቱ ወይም ተቀላቀሉ፡፡ እሳቸው የጠየቁትን 50 ሄክታር የመሬት ጥያቄ ቢፈታ ኑሮ ወልቃይት አማራ ነው አይሉም ነበር፡፡ አባታቸውም ይህንኑ በአንድ ወቅት መስክረው ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ የፌዴራል መንግስት መዳከምና የክልሎች ወጣ ወጣ ማለት የታየበት ግዜ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ በጎንደር የነበረው ጥያቄ በሁለቱም የደንበር ጥያቄ በዋናነት ደግሞ የግጭው ይመለስልን ብቻ ሳይሆን የትግራይ ተወላጆችም ከአማራ ክልል የማስወጣት፣ የማባረር፣ ንብረቶቻቸውን የመውረስና የማቃጠል እንዲሁም የመግደል ዘመቻ እየተካሄደ ነበር፡፡ ብዙ የትግራይ ተወላጆች ለዘመናት ያፈሩት ሀብት ትተው ከጎንደር ከተማና አካባቢውን እንዲሰደዱ፣ እንዲገላቱ እና እንዲሞቱ ተደረገ፡፡ መውጫ አጥተው በሱዳን በኩል ወደ ሑመራ እንዲገቡ ተደረገ፡፡ ከሰላማዊ ሰው አልፎም ብዙ የፌደራል ፖሊስ አባላት በጎንደር ተገደሉ፡፡ በዚህ ጊዜ በአቶ ሃይለማርያም የሚመራው የፌደራል መንግስት ሁኔታዎችን ለማብረድም ይሁን ለመፍታት አቅሙ ተዳክሞ ታየ፡፡ የትግራይ ህዝብና የክልሉ መንግስት ቁጣ እየጨመረ እና ሁኔታዎችን ቶሎ ተብሎ ካልተፈታ ወደ ባሰ ግጭት ሊያመራ እንደሚችል እና መፍትሄ እንዲሰጠው በተለያዩ አቅጣጫዎች ጥያቄዎች ለፌዴራልና ለሁሉቱም ክልል መንግስታት ቀረቡ፡፡ በመጨረሻም የሀገር ሽማግሌዎችና ኮሚቴ በማቋቋም የግጨው ችግር ለመፍታት በጎንደርም በመቐለም ህዝቡን ያሳተፈ ስብሰባ ተካሄደ፡፡ ሁለቱም ክልሎች ያሳተፈ የመስክ ዳሰሳ በማድረግም ለውይይት ቀረበ፡፡ የግጨው ችግሩም ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ለመፈታት ተስማሙ፡፡ በጥናቱ መሰረትም በ2008 ዓ/ም መጨረሻ አከባቢ የሁለቱም ክልል መንግስታት መሪዎች፣ ሽማግሌዎችና ኮሚቴዎች በተስማሙበት መሰረት ችግሩ ተፈታ፡፡ የሁለቱም ክልሎች ርእሳነ መስተዳድሮች የነበሩትን አቶ አባይ ወልዱ ከትግራይ፣ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ከአማራ ክልል የግጨው ጥያቄ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ በሕገመንግስት መሰረት በስምምነት ፈቱት፡፡ በፊርማቸው አረጋግጠው ዘጉት፡፡ ለሁሉም ለሚመለከታቸው የፌዴራል፣ ለአካባቢውን አስተዳደር እና ህዝቦች ችግሩ መፈታቱን በግልፅ ተነገራቸው፡፡ በሁለቱም ክልል የሚገኙት መገናኛ ብዙሃንም ለህዝባቸው አስታወቁ፡፡ ይህንን ዶክሜንት በሁለቱም

ክልሎች ለታሪክ እና ለምስክርነት ተቀምጧል (በአማራ በኩል የክልሉ መሪዎች ሆን ብለው ካላቃጠሉትና ካላጠፉት በስተቀር)፡፡ ሆኖም የግጨው ጥያቄ በዚህ መልኩ ቢፈታም ሕወሓትና የትግራይ ህዝብ የተዳከመ በመሰላቸው ግዜ ደግሞ  ጥያቄአቸው በማስፋት ወደ ወልቃይት ይመለስን ጦርነት ገቡ ብቻቸው ሳይሆን ጠላትን አሰባስበው በታሪክ ይቅር የማይባለውን በደል አደረሱበት::

እነዚህ ከለይ የቀረቡት የታሪክና ማሕበራዊ መስረጃዎች አብዛኛዎቹ በተለያዩ የታሪክና የፖለቲካ እንዲሁም የማሕበረሰብ ተመራማሪዎችና ፀሃፊያን በተለያዩ ወቅት የቀረቡ ቢሆን እንደዚህ አንድላይ በማጠቃለል በማቅረብ የመጀመሪያ ይመስለናል:: ስለዚ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የታሪክ እና ማሕበራዊ ማስረጃዎች የትግራይ ግዛት ከጥንት ጀምሮ እስከ የት እንደነበረ ያረዳሉ:: አልፎም አሁን ለሚነሱት ጥያቄዎች በተወሰኑ መልኩ መልስ የሰጠ ፅሁፍ ይመስለናል::